
መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ።



በግእዝና ፡ በአማርኛ ።

አ·ኦ· ፲፱፻፺፮ ዓ·ም·


መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት።



በግእዝና ፡ በአማርኛ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲፩ኛው ፡ ዘመነ ፡ ፓትርያርክነት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታተመ።

አሳታሚ ፡– ትንሣኤ ፡ ማኅተሚያ ፡ ድርጅት፡
አ·አ· ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ·ም



ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ምስለ ፡ ፍቁር ፡ ወልዳ።



ወሕዝብሰ ፡ እለ ፡ ይመርሑ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወእለሂ ፡ ይተልዉ ፡ ይጸርሑ ፡ ወይብሉ ፡ ሆሣዕና ፡
ለወልደ ፡ ዳዊት ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ።

ሕዝቡ፡ ግን፡ የቀደሙትም፡ የተከተሉትም፡ ሆሣዕና፡ ለዳዊት፡ ልጅ፤ በእግዚአብሔር፡
ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው፤ ሆሣዕና ፡ በአርያም፡ እያሉ ፡ ይጮሁ ፡ ነበር።

መ ል እ ክ ት

“እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ ፍስሐሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን”

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደስታዋ ፡ ዛሬ ፡ ደረሰ ፤ ተፈጸመ።

እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ሥርዓተ ፡ ጽሕፈት ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብራና ፡ እየተጻፈ፡ በዘመናዊው ፡ ኅትመት ፡ በወረቀት ፡ እየታተመና ፡ እየተባዛ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ሰፊ፡ አገልግሎት ፡ ሲሰጥበት ፡ የኖረ ፡ መሆኑ ፡ ይታወቃል።

ይሁን ፡ እንጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ በየዓመቱ ፡ የሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎትና ፡ ስግደት ፡ ሲፈጸም ፡ በሚነበብበት ፡ ሰዓት ፡ ካህናቱ ፡ ይልቁንም ፡ የምሥጢሩን ፡ ስፋትና፡ ጥልቀት ፡ የተገነዘቡ ፡ መምህራኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግእዙ ፡ በአማርኛ ፡ ተተርጉሞ ፡ ለሁሉ ፡ እንዲሠራጭ፡ ቢደረግ ፡ ውሉደ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑ ፡ ምዕመናን ፡ በሚረዱት ፡ ቋንቋ ፡ እየተጠቀሙበት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ሥርዓት መጠበቅ ፤ ለትምህርተ ፡ ሃይማኖታችን ፡ መስፋፋት ፡ በአጠቃላይ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ መግቦት ፡ ዕድሉ ፡ ሰፊ ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ አስፈላጊነቱንና ፡ ጠቃሚነቱን ፡ በማጉላት ፡ አስተያየታቸውን ፡ ሲሰጡበት ፡ እንደኖሩ ፡ ግልጽ ፡ ነው።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ በአንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት፡ በአማርኛ ፡ ከታተሙት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ምንባቡ ፡ ካለበት ፡ እየተፈለገና ፡ በጥቅስ ፡ መልክ ፡ እየተውጣጣ ፡ ከሞላጎደል ፡ ሲነበብ ፡ መቈየቱ ፡ ይታወሳል።

ነገር ፡ ግን ፡ በግብረ ፡ ሕማማት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ምንባባት ፡ ሁሉ ፡ ስለማያካትትና ፡ በተለይም ፡ ጥንታውያን ፡ አባቶቻችን ፡ ሊቃውንት ፡ ግእዝ ፡ በግእዝ ፡ የተረጐሟቸውን ፡ ትንቢታዊ ፡ ምሥጢራት ፡ ትርጓሜና ፡ ተግሣፃት ፡ እንዲሁም ፡ የድጓረ ፡ ወንጌል ፡ ምንባባት በአማርኛ ፡ የተተረጐሙ፡ መጻሕፍት ፡ ስለ ፡ አልነበሩ ፡ የመጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ ከግእዝ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ተተርጕሞ ፡ መቅረብ፡ የሁሉም ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ከፍተኛ ፡ ምኞትና ፡ ፍላጎት ፡ ሆኖ ፡ ይጠበቅ ፡ እንደነበረ ፡ ይታመናል።

“ጊዜ ፡ ገቢር ፡ ለእግዚአብሔር” ፡ እንደሚባለው ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ በሊቀ፡ መዘምራን ፡ ላዕከ ፡ ማርያም ፡ ወ/ኢየሱስ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቀረበው ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባዔ ታይቶና ፡ ተመርምሮ ፡ በማኅተሚያ ፡ ድርጅታችን ፡ አማካይነት ፡ እንዲታተም ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ከተገነዘብን ፡ ዓመታት ፡ ተቈጥረዋል። ይሁን እንጂ “ለሁሉም ፡ ጊዜ ፡ አለው” ፡ እንደተባለው ፡ የተመኘነው ፡ ተፈጽሞ ፡ ስናይ ፡ ለደስታችን ፡ ወሰን ፡ አይኖረውም።

ስለሆነም ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ በግእዝ ፡ ብቻ ፡ ሲሠራበት ፡ የኖረው ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በዕለታትና ፡ በሰዓታት ፡ የተከፈለ ፡ እንጅ ፡ ምዕራፍ ፤ ክፍል ፡ እና ፡ ቁጥር ፡ አልነበረውም። በመሆኑም ፡ ከብሉያትና ፡ ከሐዲሳት ፤ ከመጻሕፍተ ፡ ሊቃውንትና ፡ ድርሳናት ፡ የተውጣጣ ፡ እስትጉዕ ፡ እንደመሆኑ፡ መጠን ፡ በትምህርት ፡ ሰጭነቱና ፡ በበጎ ፡ መሪነቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለምዕመናን ፡ የሚሰጠውን ፡ ሰፊ፡ አገልግሎት ፡ በመገንዘብ ፡ ለአገልግሎትና ፡ ለአጠቃቀሙ ፡ አመች ፡ በሚሆን ፡ መንገድ ።

ሀ· ምዕራፍ፣

ለ· ክፍል፣

ሐ· የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቍጥር ፡ እንዲኖረው ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ ተደርጓል።

ቀደምት ፡ አባቶች ፡ ለመጻሕፍቶቻችን ፡ ምዕራፍ ፤ ቍጥር፣ አርእስትና ፡ ጎዳግ፣ ለሥነ–ጽሕፈቱ ፡ እድገት ፡ መልከና ፡ ውበት ፡ እየሰጡ ፡ እንዳቈዩት ፡ ሁሉ ፡ ይህም ፡ መነሻና ፡ መድረሻውን፡ በማወቅ ፡ ግእዙንና ፡ አማርኛውንም ፡ ለመለየትና ፡ አነጻጽሮ ፡ ለማገናዘብ ፡ እንደሚረዳ ፡ ታምኖበት፡ ነው።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ በብራናም ፡ ሆነ ፡ በወረቀት ፡ የታተሙት ፡ የግብረ ፡ ሕማማት ፡ መጻ ሕፍት፡ በቤተ፡ ክርስቲያናችን ፡ አገልግሎት ፡ ጊዜ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አምጥቶ ፡ ለማንበብ ፡

በመፈለግና ፡ መጻሕፍቱን ፡ በማገለባበጥ ፡ ጊዜ ፡ ከመውሰዱም ፡ በላይ ፡ የንባቡን ፡ አቀማመጥ ፡ ጠባይ ፡ የሚያውቁ ፡ አባቶች፡ ካልተገኙ ፡ በስተቀር ፡ አውጥቶ ፡ ለማንበብ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ እንደነበር ፡ የሚታወስ ፡ ነው።

አሁን ፡ ግን ፡ የአፈጻጸም ፡ ችግር ፡ እንዳያመጣ ፡ የአባቶችን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ የተከተለና ፡ ወጥ ፡ የሆነ፣ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ በየዓመቱ ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ በተግባር ፡ እየተጠቀመችበት ፡ በአለው ፡ መሠረት ፡ በየሰዓቱ ፡ መጀመሪያ ፡ የሚገኙትን ፡ ምንባባት ፡ ከአሪትና ፡ ከነቢያት ፡ የተውጣጡት ፣ በመጀመሪያ፡ ክፍል ፤ ከሊቃውንት ፣ ከድርሳናት ፣ ከተግሣፃትና ፡ ከተአምራት፡ የተውጣጡ ፡ በሁለተኛ ፡ ክፍል ፤ ቅድመ ፡ ወንጌል ፡ ድጎረ ፡ ወንጌል ፣ ጽንዐ ፣ቲና ፡ እስከ ፡ ማኅተመ ፡ ጸሎት፡ (የየሰዓቱ ፡ የጸሎት ፡ ፍጻሜ) ፡ ያለውን ፡ በሦስተኛ ፡ ክፍል ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ምዕራፉ፡ ግን ፡ የጸሎትና ፡ የስግደት ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ሰዓቶችን ፡ (ጊዜያትን) ፡ የሚከፍል ፡ ሆኖ ፡ ተዘጋጅቷል። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ከ፲፱፻፶ ፡ እስከ ፡ ፳፻፹ ፡ ዓ.ም. የበዓላትና ፡ የአጽዋማት ፡ የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ (ማውጫ) ፡ እንዲኖረው ፡ ተደርጓል።

ሆኖም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንደአስፈላጊነቱ ፡ ክፍሉ ፡ ከሦስት ፡ በላይ ፡ ክፍል ፡ ፬፡ ክፍል ፡ ፭፡ እና ፡ ክፍል ፡ ፮ ፡ ድረስ ፡ ሆኖአል። በዐዋትወ ፡ ዜማም ፡ በኩል ፡ የቤተ ፡ ልሔምንና ፡ የዙርአባን፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተል፡ ተደርጓል።

እንግዲህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ ከጥንተ ፡ ስሙ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ እንደምንረዳው ፡ ራሱ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ "አንሰ ፡ ሰባሕኩከ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ፈጺምየ ፡ ግብረ ፡ ዘወሀብከኒ ፡ ከመ፡ እግበር፣" (ዮሐ ፡ ፲፯፡፬) ፤ አደርገው ፡ ዘንድ ፡ የሰጠኸኝን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሜ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አከበርኩህ ፡ (ገለጽኩህ) ፡ ሲል ፡ እንደተናገረው ፡ በጅሺ ፡ ከጅ፻ ፡ ዘመን ፡ ከልጅ ፡ ልጅህ ፡ ተወልጄ ፡ በመስቀል ፡ ተሰቅዬ ፡ ሙቼ ፡ አድንኻለሁ ፡ ያለውን ፡ የተስፋ ፡ ቃሉን ፡ ለመፈጸም ፡ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወርዶ ፣ ከድንግል ፡ ማርያም፡ ተወልዶ ፣ እስከ ፡ ዕርገቱ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የፈጸማቸውን ፡ ሥራዎቹን፡ በማስታወስ ፡ ቸርነቱንና ፡ ችሮታውን ፡ የምናስብበት ፡ ታላቅና ፡ ክቡር ፡ የሆነ ፡ መንፈሳዊ፡ መመሪያችን፡ ነው።

የክርስቲያን ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሰሙነ፡ ሕማማት ፡ መሠረተ ፡ ድኅነት ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመገኘት፣ በፍጹም፡ ትጋት ፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደትና ፡ በአስተብርኮት ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራና ፡ አገልግሎት ፡ ሲፈጽም ፡ ይሰነብታል። ይህም ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ግዴታ ፡ ነው።

በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ አዘጋጁን ፤ የሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ አባላትን፤ በተለይም ፡ የማላተሚያ ፡ ድርጅቱን ፡ ኃላፊዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንና ፡ በተጠቃሚዎቹ ፡ ሊቃውንት ፣ ካህናትና ፡ ምእመናን ፡ ስም ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናለን።



መቅድም

የክርስቲያን ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በየዓመቱ ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ ራሱን ፡ ከፈቃደ ፡ ሥጋና ፡ ከክፉ፡ ነገር ፡ ከልክሎ ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በመገኘት ፡ የሚተላለፉትን ፡ መልእክታት ፡ በመከታተልና በመሳተፍ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደትና ፡ በአስተብርኮት ፡ ይሰነብታል።

ሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ የሚባለውም ፡ ከዐቢይ ፡ ጾም ፡ መጨረሻ፡ ከሆሣዕና ፡ ዋዜማ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ባሉት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ የተባለበትም ፡ ምክንያት ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ አስቀድሞ፡ የጌታችን ፡ የምሥጢረ ፡ ሕማማቱ ፡ ነገር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጾለት ፡ "ውእቱ፡ ነሥአ ፡ ደዌነ ፡ ወያረ ፡ ሕማመነ" ፡ እርሱ ፡ በእውነት ፡ ደዌያችንን ፡ ተቀበለ፡ ሕማማችንንም ፡ ተሸከመ ፡ ሲል ፡ እንደተናገረው ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለእኛ ፡ ድኅነት ፡ በፈቃዱ ፡ ሕማማተ ፡ መስቀልን ፤ በትዕግሥት ፡ በመሸከም ፡ ማህየዊ ፡ ሞቱ ፡ በመስቀሉ ፡ የተፈጸመበት፡ በመሆኑና ፡ እኛም ፡ መከራ ፡ መስቀሉን ፡ የምናስብበት ፡ ስለሆነ ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ተብሎአል። (ኢሳ ፡ ፶፫፡ ፬። ማቴ ፡ ፰፡ ፲፯።)

መሠረቱና ፡ ታሪካዊ ፡ አመጣጡም ፡ ከአባቶቻችን ፡ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ ነው ። ይኸውም፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሥቶ ፡ ለሐዋርያት ፡ እየተገለጸ ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳንንና ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሲያስተምራቸው ፡ ቈይቶ ፡ በአርባ፡ ቀኑም ፡ ሐዋርያትን ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ሹሟቸውና ፡ ባርኳቸው ፡ አርጓል። (ማር· ፲፮፡ ፲፱። ሉቃ· ፳፬፡ ፶፩። የሐዋ· ሥራ ፡ ፩፡፱)

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ካሉ ፡ ምዕመናን ፡ ጋር ፡ ጾም ፡ መጾምንና ፡ ትንሣኤውን፡ ማክበር፡ ጀመሩ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ተሰብስበው ፡ በደነገጉት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ስለ ፡ ሰሙነ፡ ሕማማት ፡ "ወአንትሙሰ ፡ ተዐቀቡ ፡ ወግበሩ ፡ ተዝካረ ፡ ሕማማቲሁ" ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ጠብቃችሁ ፡ የመከራ፡ መስቀሉ ፡ መታሰቢያ ፡ የሆነውን ፡ ሕማማቱን ፡ አድርጉ፡ አከብሩ ፡ ሲሉ ፡ አዝዘዋል። (ትእዛዝ ፡ ፴፭)

ሆኖም ፡ ሐዋርያት ፡ ለስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ይፋጠኑ ፡ ነበረና ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ሁሉ ፡ ጊዜውን ፡ አልወሰኑትም ፡ ነበር። ከሐዋርያት ፡ ቀጥለው ፡ የተነሱ ፡ ሊቃውንትም ፡ ቢሆኑ ፡ እንደዚሁ ፡ በዐተ ፡ ጾምን ፡ ከጥር ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ የካቲት ፡ ፭፭ ፡ ቀን ፡ ከጾሙ ፡ በኋላ ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ ደግሞ ፡ ከዐቢይ ፡ ጾም ፡ ለይተው ፡ ከመጋቢት ፡ ፳፪ ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ በመጾም ፡ መጋቢት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ትንሣኤውን ፡ ያከብሩ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሥርዓት ፡ ሲያያዝ ፡ እስከ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ዘመን ፡ ደረሰ ።

ከ፩፻፹፰ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴ ፡ ዓ·ም ፡ የነበረው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በአዘጋጀው ፡ የጊዜ ፡ መቁጠሪያ ፡ (ባሕረ ፡ ሐሳብ) ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ከዐቢይ ፡ ጾም ፡ ቀጥሎ ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኖአል። ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በቀመረ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ዓመታትን ፡ በንዑስ ፡ በማዕከላዊና ፡ በዐቢይ ፡ ቀመር ፡ እየቀመረች ፡ አጽዋማት ፡ የሚገቡበትንና ፡ በዓላት ፡ የሚውሉበትን ፡ ጊዜ ፡ ለምዕመናን ፡ ታሳውቃለች።

ስለሆነም ፡ የሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎትና ፡ አገልግሎት ፡ ሁኔታ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ሥርዓተ፡ አምልኮት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ቢሆንም ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ ሥርዓት ፡ የያዘ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ የተሰኘው ፡ መጽሐፍ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ ከጌታ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፲፬፻ኛው ፡ ምዕት ፡ ዓመት፡ ነው።

ከ፩፯፫፻፺ ፡ እስከ ፡ ፩፯፫፻፹ ፡ ዓ·ም ፡ የነበሩት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ብርሃነ ፡ ዐዜብ ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ እንደተረጎሙት ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በግእዝ ፡ ብቻ ፡ ታትሞ ፡ በነበረው ፡ የግብረ ፡ ሕማማት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጠአል።

የመጽሐፉ ፡ ስያሜም ፡ ከጥንተ ፡ ስሙ ፡ ጀምሮ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ እንደሚባል ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ክፍል ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ። ለዚሁም ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ምክንያት ፡ እንዳለው ፡ ይታመናል። ሊቀ ፡ ነቢያት ፡ ሙሴ ፡ "በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ"፤ በመጀመሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጠረ ፡ (ዘፍ፡ ፩፡፩) ፡ ያለውንና ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ "ዘገብረ ፡ ሰማያተ ፡ በጥበቡ" ፡ ሰማያትን ፡ በጥበቡ ፡ የሠራ ፡ (የፈጠረ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነውና ፡ አመስግኑት። (መዝ ፡ ፻፴፭፡ ፭) ፤ ሲል ፡ እንደተናገረው፡ ቀዳማዊ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ብዙኃት ፡ ፍጥረት፡ ከባሕርይ ፡ አባቱ ፡ አብ፡ ከባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕልው ፡ ሆኖ ፡ በረቂቅ ፡ ጥበቡ ፡ ዓለማትንና ፡ ፍጥረታትን ፡ ሁሉ ፡ በየወገኑ ፡ ፈጥሮ ፡ እንደየባሕርያቸው ፡ በቸርነቱ፡ መግቦና ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ እንደመሆኑ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ዘመንም ፡ ራሱ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ዓለምን ፡ ከፈጠረበት ፡

በሚበልጥ ፡ ጥበቡ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሥጋን ፡ ለብሶ ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ተወልዶ ፡ አዳምን ፡ ከነዘሩ ፡ እንደገና ፡ በአዲስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ወደቀደመው ፡ ክብሩና ፡ ቦታው ፡ እንደመለሰው ፡ ያመለክታል ፤ (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፯። ራዕ ፡ ፳፩ ፡ ፭። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፲፩።)

ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፡ "ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሰመየ ፡ ሕማማተ ፡ ወልዱ ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ" ፡ የልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሕማማት ፡ ክብርና ፡ ምሥጋና ፡ ጌትነት ፡ ብሎ ፡ የጠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ያለው ፡ ስለዚህ ፡ ነው።

ምሥጢራዊ ፡ ዓላማውም ፡ ጌታ ፡ በሕማሙ ፡ ሕማማችንን ፡ በሞቱ ፡ ሞታችንን ፡ በትንሣኤው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነፃነትንና ፡ ክብርን ፡ ያጐናጸፈን ፡ መሆኑን ፡ ከማስገንዘቡም ፡ በላይ ፡ በባሕርዩ ፡ መከራና ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ አምላክ ፡ መሆኑ ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ በየአንዳንዱ ፡ ቀን ፡ ይነበባል፤ ይተረካልም።

መጽሐፉ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ነገረ ፡ መስቀልን ፡ ምሥጢረ ፡ ቍርባንንና ፡ ምሥጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ የያዘ ፡ እጅግ ፡ ጥልቅና ፡ ምጡቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በየጊዜው ፡ በብራና ፡ እየተጻፈ ፡ ሲሠራበት ፡ ለ፮፻ ዓመታት ፡ ያህል ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ.ም. በመምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ብርሃነ ፡ መስቀል ፡ (ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሉቃስ)፡ አቅራቢነት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ፈቃድ ፡ ታትሞ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ እንዲዳረስ ፡ ተደርጎአል ። የመጀመሪያው ፡ እትም ፡ ስለ ፡ አለቀ ፡ እንደገና ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ከ፴ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፹፪ ፡ ዓ.ም. በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፈቃድ ፡ በግእዝ፡ ብቻ ፡ ታትሞ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ሆኖአል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አገልግሎቱ ፡ ምዕመናንን ፡ ስለ፡ አላሳተፈ ፡ የተሟላ ፡ አልነበረም ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚሰማው ፡ በአማርኛ ፡ ቋምር ፡ ቢታተምና፡ ቢቀርብ ፡ አገልግሎቱ ፡ የበለጠ ፡ እንደሚሆን ፡ ስለታመነበት ፡ በሊቀ ፡ መዘምራን ፡ ላዕከ ፡ ማርያም ፡ ወ/ኢየሱስ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ ተመርምሮ ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ እንዲታተም ፡ ተደርጎአል።

በዚህ ፡ መሠረት ፡ የሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ጸሎትና ፡ አገልግሎት ፡ ጠቅላላ ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፈ፡ ግብረ፡ ሕማማት ፡ በየክፍሉ ፡ ተጽፎ ፡ ስለሚገኝ ፡ ካህናትም ፡ ምዕመናንም ፡ መጽሐፉን ፡ በመያዝ፡ ሥርዓቱን ፡ ለመከታተል፡ ያመቻል ፡ የሚል ፡ ጽኑእ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መቅረቡ ፡ በተለይ ፡ ምዕመናንና ፡ ምዕመናት ፡ ጸሎቱን ፡ በትጋት ፡ እንዲካፈሉ ፤ ትምህርቱን ፡ እንዲከታተሉ ፤ ምሥጢሩንም ፡ እንዲያስተውሉና ፡ በረከቱን ፡ እንዲሳተፉ ፡ ከማስቻሉም ፡ በላይ ፡ መሪያቸው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በፍጹም ፡ እምነትና ፡ ፍቅር ፡ እንዲከተሉ ፡ ጥሪውን ፡ ያስተላልፋል ፡ ይቀሰቅሳል። ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ "ለዚህ ፡ ተጠርታችኋል፡ ክርስቶስም ፡ እኮ ፡ ፍለጋውን ፡ ትከተሉ ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱን ፡ ሊተውላችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ መከራ፡ ተቀብሎአል" ፡ ያለው ፡ ስለዚህ ፡ መሆኑን ፡ ያስታውሰናልና ፡ ነው። (፩ኛ ፡ ጴጥ፡ ፪፡፳፩።)

ስለዚህ ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፤ ሊቃውንት፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፈለግ ፡ በመከተል ፡ ሕግንና ፡ ሥርዓትን ፡ ጠብቀው ፡ ያስተላለፉልንን ፡ የሕይወተ ፡ ሥጋና ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ መዓዛ ፡ የሆነው ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታትሞ ፡ በተገቢ ፡ መልኩ ፡ የቀረበ ፡ ስለሆነ ፡ መጠቀሙ ፡ የኛ ፡ ፋንታ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ፡ እንላለን ።

"ወይእዜኒ ፡ አኀዊነ ፡ ጸልዩ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ይሩጽ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሰባሕ ፡ በከመ ፡ በኀቤክሙ"፤ (፪ኛ ፡ ተሰ· ፫፡፩) ።

ትንሣኤ ፡ ማሳተሚያ ፡ ድርጅት ።
አ·አ ፲፱፻፸፮ ፡ ዓ·ም

ምዕራፍ	አ ር ዕ ስ ት	ከ	እስከ
፩	ዘማኅትመ ፡ ሞሣዕና።	፩	፴፱
፪	ዘዕለተ ፡ ሞሣዕና ፡ (እሑድ)።	፴፱	፶፯
፫	” ” ”	፶፯	፷፰
፬	” ” ”	፷፰	፸፱
፭	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘሰኑይ።	፸፱	፹፱
፮	ዘ፪ ፡ ” ” ”	፹፱	፺፯
፯	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፺፯	፻፮
፰	ዘ፬ ፡ ” ” ”	፻፮	፻፳፫
፱	ዘ፲ወ፩ ” ” ”	፻፳፫	፻፴፪
፲	በጊዜ ፡ ነግህ ፡ (ዘሰኑይ)።	፻፴፪	፻፵፭
፲፩	ዘ፫ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘሰኑይ።	፻፵፭	፻፶
፲፪	ዘ፮ ፡ ” ” ”	፻፶	፻፶፱
፲፫	ዘ፱ ፡ ” ” ”	፻፶፱	፻፷፯
፲፬	ዘ፲ወ፩ ” ” ”	፻፷፯	፻፸፪
፲፭	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘሠሉስ ።	፻፸፪	፻፸፰
፲፮	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፻፸፰	፻፹፬
፲፯	ዘ፮ ፡ ” ” ”	፻፹፬	፻፺
፲፰	ዘ፱ ፡ ” ” ”	፻፺	፻፺፮
፲፱	ዘ፲ወ፩፡” ” ”	፻፺፮	፻፺፱
፳	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘሠሉስ ።	፻፺፱	፪፻፲
፳፩	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፪፻፲	፪፻፲፭
፳፪	ዘ፮ ፡ ” ” ”	፪፻፲፭	፪፻፳፪
፳፫	ዘ፱ ፡ ” ” ”	፪፻፳፪	፪፻፳፰
፳፬	ዘ፲ወ፩፡” ” ”	፪፻፳፰	፪፻፴፫
፳፭	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘረቡዕ ።	፪፻፴፫	፪፻፴፰
፳፮	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፪፻፴፰	፪፻፵፪
፳፯	ዘ፮ ፡ ” ” ”	፪፻፵፪	፪፻፵፮
፳፰	ዘ፱ ፡ ” ” ”	፪፻፵፮	፪፻፶፩
፳፱	ዘ፲ወ፩፡” ” ”	፪፻፶፩	፪፻፶፭
፴	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘረቡዕ።	፪፻፶፭	፫፻፩
፴፩	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፫፻፩	፫፻፭
፴፪	ዘ፮ ፡ ” ” ”	፫፻፭	፫፻፲
፴፫	ዘ፱ ፡ ” ” ”	፫፻፲	፫፻፲፭
፴፬	ዘ፲ወ፩፡” ” ”	፫፻፲፭	፫፻፳፩
፴፭	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘሐሙስ ።	፫፻፳፩	፫፻፳፮
፴፮	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፫፻፳፮	፫፻፴፪
፴፯	ዘ፮ ፡ ” ” ”	፫፻፴፪	፫፻፴፮
፴፰	ዘ፱ ፡ ” ” ”	፫፻፴፮	፫፻፵፩
፴፱	ዘ፲ወ፩፡” ” ”	፫፻፵፩	፫፻፵፭

ምዕራፍ፡	አ ር ዕ ስ ት፡	ከ	እስከ፡
፩	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘሐሙስ ።	፬፻፸፫	፬፻፹፭
፩፩	ዘ፪ ፡ ” ” ”	፬፻፹፬	፬፻፹፰
፩፪	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፬፻፹፱	፭፻፲፩
፩፫	ዘ፬ ፡ ” ” ”	፭፻፲፪	፭፻፴፪
፩፬	” ” ” ”	፭፻፴፫	፭፻፴፮
፩፭	ዘፕወ፩፡” ” ”	፭፻፴፯	፭፻፵
፩፮	ዘፕወ፩፡” ” ”	፭፻፵፩	፭፻፵፬
፩፯	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘዓርብ።	፭፻፵፭	፭፻፵፱
፩፰	ዘ፪ ፡ ” ” ”	፭፻፵፱	፭፻፶፫
፩፱	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፭፻፶፫	፭፻፶፯
፪፩	ዘ፬ ፡ ” ” ”	፭፻፶፯	፭፻፷፩
፪	ዘፕወ፩፡” ” ”	፭፻፷፩	፭፻፷፭
፪፩	ዘዓርብ ፡ ጽባሕ ፡ (ነግህ)	፭፻፷፭	፭፻፸፩
፪፪	ዘ፪ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘዓርብ።	፭፻፸፩	፭፻፸፮
፪፫	ዘ፫ ፡ ” ” ”	፭፻፸፮	፭፻፹፪
፪፬	ዘ፬ ፡ ” ” ”	፭፻፹፪	፭፻፹፮
፪፭	ዘፕወ፩፡” ” ”	፭፻፹፮	፭፻፺
፪፮	ዘፕወ፪፡” ” ”	፭፻፺	፭፻፺፭
፪፯	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘቀዳሚት ።	፭፻፺፭	፮፻፫
፪፰	ዘ፪ ፡ ” ” ”	፮፻፫	፮፻፰
፪፱	ዘቀዳም ነግህ ።	፮፻፰	፮፻፲
፫	ዘ፩ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘቀዳሚት ።	፮፻፲	፮፻፲፬
፫፩	ዘ፪ ፡ ” ” ”	፮፻፲፬	—
፫፪	ዘ፫ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ዘእሑድ ።	፮፻፲፬	፮፻፲፰
፫፫	ዘፕወ፪ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘእሑድ ።	፮፻፲፰	፮፻፳፫
፫፬	ጸሎት ፡ ዘሰብዓቱ ፡ ጊዜያት ።	፮፻፳፫	፮፻፳፰
—	ከፕ፱፻፶ ፡ ዓ·ም· እስከ ፡ ፳፻፹፱ ፡(ፌሺሕ ፡ ፹፱ ፡ ዓ·ም·)የአጽዋማትና ፡ የበዓላት ፡ ማውጫ።	፮፻፳፰	፮፻፴፯

መጽሐፈ፡ግብረ፡ሕማማት።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።

የሆሣዕና፡ዋዜማ።

ምዕራፍ፡፩።

ትዕዛዝ፤

ይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ቅድስት ፡ በማኅትወ ፡ ሰንበት፡ ዘሆሣዕና። ወይበል ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘየዐቢ ፡ በጥዑም፡ዜማ፡ግዕዛዊ፡ዘውእቱ፡ርቱዕ፡ዘንተ፡ ቃለ፡ኪዳን፡ቅዱስ። ወእምዝ፡ይትልዉ፡ዘንተ፡ አሠረ፤ ኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ እስከ ፡ ተፍጸሜቱ ፡ ይበሉ። በከመ፡ሥርዓት፡ዘይደሉ።

ዋዜማ፡ዘሆሣዕና።

በኧሃሌ ፡ ሉያ ፡ በእምርት ፡ ዕለት ፡ በዓልነ ፡ ንፍጉ፡ ቀርነ ፡ በጽዮን ፡ ወስብኩ ፡ በደብረ ፡ መቅደስየ። እስመ ፡ ይቤ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ በዓለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ ቡሩክ ፡ አንተ፡ንጉሠ፡እሥራኤል።

ምልጣን፡ገሊ፡ከማሁ።

እስመ ፡ ይቤ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ በዓለ፡ እግዚአ ብሔር፡ ሆሣዕና፡ በአርያም፡ ቡሩክ፡ አንተ፡ ንጉሠ፡ እሥራኤል። ቡሩክ፡ አንተ፡ ንጉሠ፡ እሥራኤል። (በኧ)፡ ይብሉ፡ ሆሣዕና፡ በአርያም፡ ለንጉሥ፡ ለወልደ፡ ዳዊት፡ ይብሉ፡ ሆሣዕና፡በአርያም።

እግዚአብሔር ፡ ነግሠ። ተፈሥሑ ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ዘረድእነ ፡ ወየብቡ ፡ ለአምላክ ፡ ያዕቆብ፡ ንፍጉ ፡ ቀርነ ፡ በጽዮን ፡ በዕለተ ፡ ሠርቅ፡በእምርት፡ዕለት፡በዓልነ።

(በኧ)፡ ደቂቅኒ ፡ እንዘ ፡ ይጸርሑ ፡ ወሕዝብኒ ፡ ኪያሁ፡ይሴብሑ፡ደቂቅኒ፡እንዘ፡ይጸርሑ።

ክፍል፡፩።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ፡አምላክ፡

፩፤ ንቀድም ፡ በረድኤተ ፡እግዚአብሔር ፡ ወበሥ ምረቱ፡ወንጽሕፍ፡ዘንተ፡መጽሐፈ፡ቅዱሰ፡ ዘይደሉ፡አንብቦቱ፡በበ፡ጸታሁ፡በመዋዕለ፡ ሰሙን ፡ ክብርት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሰሙነ ፡ ፍሥሕ፡ እምኦሪት ፡ ወእምነቢያት ፡ ወመዝሙረ ፡ዳዊት ፡ ወወንጌላት ፡ ቅዱሳት ፡ ለዘበአማን ፡በግዕ ፡ቅዱስ ፡ወጥዩቅ።

ምዕራፍ፡፩።

ትእዛዝ፤

በሆሣዕና ፡ ሰንበት ፡ ዋዜማ ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ካህናት ፡ ይሰበሰቡ።

ከእነርሳቸውም ፡ በማዕረግ ፡ የሚበልጥ ፡ አንዱ፡ በግዕዝ ፡ በሚጣፍጥ ፡ ዜማ ፡ ቅዱስ ፡ ይበል፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህናቱም፤ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ እሱን ፡ ተከትለው ፡ ሥርዓቱ፡እንደሚያዘው፡ይበሉ።

የሆሣዕና፡ዋዜማ።

በአንድ ፡ ሃሌታ ፤ የታወቀች ፡ የተረዳች ፡ በሆነች፡በዓላችን ፡በጽዮን ፡ነጋሪትን ፡ምቱ፤ በምመሰገንበትም፡ተራራ፡ስበኩ።

ይች፡ቀን ፡የእግዚአብሔር ፡በዓል ፡ናት ፡ብሎ አልና ፡ የተባረከ ፡ የእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በአርያም፡የሚኖር ፡መድኃኒት ፡አንተ ፡ነህ።

ምልጣኑም፡እንደዚሁ፡ነው።

ይች ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ናት ፡ ብሏልና፤ በአርያም ፡ ያለ ፡ መድኃኒት ፤ የተባረከ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ የተባረከ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህ።

በአምስት ፡ ለንጉሡ ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ በአርያም፡ ያለ ፡ መድኃኒት ፡ መባል ፡ ይገባዋል ፡ ይላሉ።

በእግዚአብሔር ፡ ነግሠ ፡ የሚባል ፡— በረዳን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፤ ለያዕቆብም፡ ፈጣሪ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ። በታወቀችና ፡ በተረዳች ፡ በዓላችን ፡ በወር ፡ መባቻ ፡ በመመስገኛው ፡ በጽዮን ፡ ነጋሪት ፡ ምቱ።

በኧ ፡ ሕፃናቱም ፡ እየጮሁ ፡ ሕዝቡም ፡ ከእርሳቸው ጋራ ፡ ከአርያም ፡ የተገኘ ፡ መድኃኒት ፡ እያሉ ፡ እርሱን ፡ ያመሰግናሉ።

ክፍል፡፩።

አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም፤

፩፤ መተላለፊያ ፡ በምትሆን ፡ በዚች ፡ በከበረች ፡ ሰሞን ፡ በየወቅቱ ፡ መነበብ ፡ የሚገባውን ፡ ከአሪት ፡ ከነቢያት ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙርና ፡ ከቅዱሳት ፡ ወንጌላት ፡ በጎላና ፡ በተረዳ ፡ ነገር ፡ አማናዊ ፡ ለሆነው ፡ ቅዱስ ፡ በግዕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤትና ፡ ፈቃድ ፡ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ፡አስቀድመን፡እንጽፋለን።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፪፤ ሠራዕነ ፡ በአቅልሎ ፡ ወአሕጸጽነ ፡ በፍካሬ ፡ ከመ፡ኢይኩን፡ሀኬተ፡ለዘይሰምዕ፡ዘክሮታ፡ ወይትሔደስ ፡ ውስተ ፡ ኅሊና ፡ ጸዋትዊሃ ፡ ወነገራ።	፪፤ መታሰቢን ፡ ለሚሰማው ፡ አታካች ፡ እን ይሆን፡በየረድፉ፡የሚነገረው፡ምሥጢራና ሥልቷ፡በልቡና፡እየታደሰ፡እንዲኖር፡ትር ሚውን፡በማሳነስ፡አቅልለን፡ሠራን።
፫፤ ወኢይፀራዕ ፡ ስባሔ ፡ ወውዳሴ ፡ ወዘምሮ ፡ ለመፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ዘኃረየ ፡ አግብርቲሁ ፡ እምኵሉ፡ፍጥረት፡በብዙኅ፡ሀብቱ፡ወሠናይ፡ መክፈልቱ።	፫፤ ከፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ለይቶ ፡ እኛን ፡ ባሮቹን ፡ ለመረጠ ፡ ሰውን ፡ ወዳጅ ፡ ለሆነ ፡ በብዙ ፡ ሀብቱና፡በመልካም፡ስጦታው፡ፍጹም፡ምስ ጋናውና፡ዝማሬው፡እንዳይታጐል።
፬፤ ወኢይክል ፡ ልሳን ፡ ፈክሮታ ፡ ወኢቀለም ፡ ወአጸብዕ፡ከቲቦታ፡ወኢተርጕሞታ።	፬፤ አንደበትም፡ሊተረጕማት፡ጣቶችም፡በቀለም፡ ሊጽፍዋትና፡ሊገልጹዋት፡አይችሉም።
፭፤ ወኢይክል ፡ ዘሥጋ ፡ በበንስቲት ፡ ሐግኃታ ። ወአኮ፡እለ፡በኀጢእ፡ወአኅጽሮ። ወናርምም ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ከመ ፡ ቁመት ፡ ኀጺር፡ወንኡስ።	፭፤ ሥጋ ፡ ለባሽም ፡ በየጥቂቱ ፡ ሊደነግጋት ፡ አይችልም ። ምሥጢሩንም ፡ በማጣትና ፡ በማሳጠር፡አይደለም። አጭርና፡ትንሽ፡እንደሆነ፡ቁመት፡ከእርሱ፡ የተነሣ፡ዝም፡እንበል።
፮፤ ወዛተ፡ሰሙነ፡አብጽሐክሙ፡እግዚአብሔር፡ በሥምረቱ ፡ ወረድአክሙ ፡ በገቢረ ፡ ፈቃዱ ፡ ወጼሐ፡ለክሙ፡ፍኖተ፡ረድኤቱ።	፮፤ ለዚችም፡ለሰሙነ፡ሕማማት፡በቸርነቱ፡እግዚአ ብሔር ፡ አደረሳችሁ ፤ ፈቃዱንም ፡ ለመሥራት፡ ረዳችሁ፤የረድኤቱንም፡መንገድ፡ጠረገላችሁ።
፯፤ ወባልሐክሙ ፡ እምጸላኢ ፡ ወሐሳዊ ፡ ወእምሰ ራዊቱ፡ወእምኵሉ፡ተቃርኖቱ።	፯፤ ከሐሰተኛው ፡ ጠላት ፡ ከዲያብሎስ ፡ ከሠራ ዊቱና፡ከሰልፉም፡ሁሉ፡አዳናችሁ።
፰፤ እስመ ፡ ሐገኑ ፡ ባቲ ፡ አርድእት ፡ ንጹሐን ፡ ወአበው፡ቅዱሳን፡ወጻድቃን፡ቡሩካን፡ሕገ፡ አስተዳለዉ ፡ ወአዘዙ ፡ ባቲ ፡ በሥርዓት ፡ ወሠርዕዋ ፡ ወአጽንዕዋ ፡ ወጽሕቁ ፡ ለገቢረ ፡ ይእቲ፡ወኀሠሡ፡ከመ፡ኢይትሀከይ፡መኑሂ፡ እምኔሃ፡ወአይድዑ፡ከመ፡ኢይኩን፡ዝንጋዔ፡ በምንትኒ፡ባቲ።	፰፤ ንጹሐን ፡ ሐዋርያትና ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶች ፡ ቡሩካን፡ጻድቃን፡በእርስዋ፡ሕግን፡አዘጋጁ፤ ትእዛዝም፡ሰጡባት፤ሥርዓትንም፡ሠርተው፡ አጸኑዋት። ሊሠራዋም ፡ ተጉ ፤ ከእርስዋ ፡ ማንም፡ እንዳይሰንፍ ፡ ፈለጉ ፤ በምንም ፡ በምን፡ ዝንጋታ ፡ እንዳይሆን ፡ ተናገሩ ፤ አስተማሩ።
፱፤ ወጸሐፉ ፡ ንስቲተ ፡ እምኔሃ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ መጽሐፍ፡ከመ፡ይርአይ፡ወይፈጽም፡ገድለ፡ እምኵሉ፡ሕገኒሃ። ወአኅለቁ ፡ ነገራ ፡ ወዘጸሐፉ ፡ ውስቴታ ፡ ወዘዘከሩ፡በዲድስቅልያ፡ቅድስት።	፱፤ ማንም ፡ ሰው ፡ አይቶ ፡ ከሕጓ ፡ ሁሉ ፡ ተጋድ ሎውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ፡ በጥቂቱ፡ጽፈዋል። ልዩ ፡ በሆነች ፡ በዲድስቅልያ ፡ ያወሱትንና ፡ በውስጥዋ፡የጸፉትን፡ነገርዋን፡ፈጸሙ።
ትእዛዝ፡ዘሠላሳ፡ወአሐዱ።	የሠላሳ፡አንደኛ፡ትእዛዝ።
፩፤ መፍትው፡ለክሙ፡አ፡ፍቁራን፡አኀው፡ዘተሣ የጠክሙ፡በደሙ፡ክቡር፡ክርስቶስ፡ትግበሩ፡ በዓለ፡ዕለተ፡ቅድስት፡ፋሲካ፡በኵሉ፡ጥያቄ፡ ወበለብዎ።	፩፤ ክርስቶስ ፡ በከበረ ፡ ደሙ ፡ የዋጃችሁ ፡ የተወደ ዳችሁ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ በፍጹም ፡ መረ ዳትና ፡ በማስተዋል ፡ የከበረች ፡ የፋሲካን፡ ቀን፡በዓል፡ታደርጉ፡ዘንድ፡ይገባችኋል።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፪፤ እስመ ፡ ይዔሪ ፡ መዓልታ ፡ ወሌሊታ ፡ እመ ፡ ዕሥራ፡ወኀሙሱ፡ለወርኀ፡መጋቢት።	፪፤ በመጋቢት ፡ ወር ፡ በሃያ ፡ አምስት ፡ ቀንዋና ፡ ሌሊትዋ፡ይተካከላልና።
፫፤ ጠይቁ ፡ እንከ ፡ ሐሳበ ፡ እስመ ፡ ኢሐመ ፡ እግዚእነ፡በአሐቲ፡ዓመት፡ክልኤተ፡ጊዜ።	፫፤ ጌታችን፡በአንዲት፡ዓመት፡ሁለት፡ጊዜ፡መከራ፡ አልተቀበለምና፡እንግዲህ፡ቀኖሩን፡ተረዱ።
፬፤ ወአንትሙ ፡ ተዐቀቡ ፡ ወግበሩ ፡ ተዝካረ ፡ ሕማማቲሁ፡አሐተ፡ጊዜ፡በበዓመት፡እስመ፡ በእንቲአነ፡ሞተ።	፬፤ እናንተም ፡ ተጠንቅቃችሁ ፡ የመከራውን ፡ መታሰቢያ፡በየዓመቱ፡አንድ፡ጊዜ፡አድርጉ፡ ስለእኛ፡ሙቷልና።
፭፤ ወኢትኅበሩ፡ገቢረ፡በዓል፡ምስለ፡አይሁድ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ፍቅር ፡ ማእከሌነ ፡ ወማእከ ሌሆሙ። እስመ፡እሙንቱ፡ስሕቱ፡በእበዶሙ፡ወበኢያ እምሮ ፡ ሐሳብ ፡ እንዘ ፡ ይመስሎሙ ፡ ዘይፈጽሙ።	፭፤ ከአይሁድም ፡ ጋራ ፡ በዓል ፡ በማድረግ ፡ አትተ ባበሩ ፤ በእኛና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ፍቅር ፡ የለምና። እነርሱ ፡ በስንፍናቸው ፡ የተቈጠረውንም ፡ ሱባዔ፡ባለማወቃቸው፡የሚፈጽሙ፡እየመሰ ላቸው፡ስተዋልና።
፮፤ ወበእንተዝ ፡ ኮኑ ፡ ኀሡራነ ፡ በኵሉ ፡ ምድር ፡ ወውዑአነ፡እምጽድቅ።	፮፤ ስለዚህም ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ የጐሰቈሉና ፡ ከጽድቅም፡የወጡ፡ሆኑ።
፯፤ ወአንትሙሰ ፡ ዕቀቡ ፡ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወኀሙሱ፡ለወርኀ ፡ መጋቢት ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወተሰዉ ፡ ለመጋቢት ፡ በሐሳቦሙ፡ለዐረባውያን።	፯፤ እናንተ፡ግን፡የመጋቢትን፡ወር፡ሃያ፡አምስተ ኛውን ፡ ቀን ፡ ጠብቁ ፤ ይህም ፡ በዐረቦች ፡ አቈጣጠር ፡ መጋቢት ፡ ሃያ ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ነው።
፰፤ ዕቀቡ ፡ ዘንተ ፡ ሐሳበ ፡ እምዐሠርቱ ፡ ወኀምስቱ፡ እስከ ፡ ዕሥራ ፡ ወኀሙሱ ፡ ለሠርቀ፡ሌሊት።	፰፤ ይኸንንም፡ቀኖር፡ከአሥራ፡አምስት፡እስከ፡ ሃያ፡አምስት፡የሌሊቱን፡መባቻ፡ጠብቁ።
፱፤ ወዓዲ ፡ ኢትስሐቱ ፡ ሐሳበ ፡ ፍሥሕ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ፋሲካ ፡ ክልኤተ ፡ ጊዜ ፡ በአሐዱ ፡ ዓመት ፡ ወከመ ፡ ኢይኩን ፡ ቅድመ ፡ ሆሣዕና ፡ በኢጠይቆ ፡ ሐሳብ ። ዳእሙ ፡ ይኩን ፡ ዕለተ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ቅድስት ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሰንበተ ፡ ክርስ ቲያን።	፱፤ ዳግመኛም፡የፍሥሕን፡አቈጣጠር፡አትሳቱ፤ ፋሲካ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንዳ ይሆን አቈጣጠሩን ፡ ባለመረዳት ፡ ከሆሣዕና ፡ ቀድሞ ፡ እንዳይውል ፡ የጌታችንና ፡ የመድኃኒ ታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የከበረች ፡ የትን ሣኤው ፡ ቀን ፡ በርክስቲያኖች ፡ ሰንበት ፡ በዕለተ፡ዕሁድ፡ይሁን፡እንጂ።
፲፤ ወዓዲ ፡ ይኩን ፡ ጾመ ፡ ቅድስት ፡ ፋሲካ ፡ እምሰኑይ፡እስከ፡ቀዳሚት፡ሰንበት፡ማኅትወ፡ ፋሲካ።	፲፤ የከበረች ፡ የፋሲካም ፡ ጾም ፡ ከሰኞ ፡ እስከ ፡ ፋሲካ፡ ዋዜማ ፡ እስከ ፡ ቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ይሁን።
፲፩፤ ወበሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ኢትብልዑ ፡ ወኢም ንተኒ፡ዘእንበለ፡ኀብስት፡ወማይ፡ወጼው።	፲፩፤ በሕማማትም ፡ ሰሞን ፡ ከእንጀራ ፡ ከጨውና ፡ ከውኃ፡በቀር፡ምንም፡ምን፡አትብሉ።
፲፪፤ ወተዐቀቡ ፡ በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ አጽዋም ፡ እምበሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ወሰትየ ፡ ወይን ፡ እስመ ፡ መዋዕል፡ላሕ፡ወሐዘን፡እማንቱ።	፲፪፤ በእነዚህም፡የጾም፡ቀናት፡ሥጋ፡ከመብላትና፡ መጠጥ ፡ ከመጠጣት ፡ ተጠበቁ ። የልቅሶና ፡ የሐዘን፡ወራት፡ናቸውና።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።

፲፫፤ ወፈድፋደስ፡በእሉ፡ሰዱስ፡ዕለታት፡እመ፡ቦ፡ዘይክል፡ጸዊመ፡ይትዐገሥ፡ክልኤተ፡ዕለተ፡ወእመ፡አኮ፡ዘኢይክል፡ጸዊመ፡ይጹም፡በበ፡አሐቲ፡ዕለት፡ወይትዐቀብ፡እምግባር፡እኩይ።

፲፬፤ እስመ፡ይቤ፡እግዚእነ፡ኢይክሉ፡ደቂቁ፡ለመርዓዊ፡ጸዊመ፡አምጣነ፡ሀሎ፡መርዓዊ፡ምስሌሆሙ።ወባሕቱ፡ይመጽእ፡መዋዕል፡አመ፡ይነሥእዎ፡ለመርዓዊ፡እምኔሆሙ፡ውእተ፡አሚረ፡ይጸውሙ።

፲፭፤ እስመ፡በዝንቱ፡ሰዱስ፡መዋዕል፡ነሥእዎ፡አይሁድ፡እምኔነ፡ወሰቀልዎ፡ዲበ፡ዕፅ፡ወጎለቍዎ፡ምስለ፡ጊጉያን።

፲፮፤ ወበእንተዝ፡ንኤዝዘክሙ፡ትጹሙ፡በከመ፡ገበርነ፡ንሕነ፡እምድኅረ፡ዐርገ፡እግዚእነ፡ውስተ፡ሰማያት።

፲፯፤ ወባዕዳንሂ፡መዋዕለ፡ይጹሙ፡እስከ፡ተሰዐቱ፡ሰዓት፡ዘያፈደፍድ፡ይጹም፡እስከ፡ዕርበተ፡ፀሐይ።

፲፰፤ ወዕቀቡ፡ሰዓተ፡ሌሊት፡እስከ፡ይነቁ፡ዶርሆ፡ተጋቢአክሙ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡በስብሐት፡ወበጸሎት፡እንዘ፡ታነብቡ፡አሪተ፡ወነቢያተ፡ወመዝሙረ፡ዳዊት።

፲፱፤ ወእምድኅረ፡አጥመቅምዎሙ፡አንብቡ፡መዝሙረ፡በፍርሃት፡ወበረዓድ፡ወመሀርዎሙ፡ለሕዝብ፡በቍዔተ፡ለነፍሳቲሆሙ።

፳፤ ወሰአልዎ፡ለእግዚአብሔር፡ይትመየጡ፡እስራኤል፡ውስተ፡ንስሓ፡ወይድኅኑ፡እምዕልወት፡እስመ፡መኰንን፡ተጎዕበ፡እዴሁ፡ወይቤ፡ንጹሕ፡አነ፡እምደሙ፡ለዝ፡ብእሲ፡ጻድቅ።

፳፩፤ ወእስራኤልሰ፡ከልሑ፡እንዘ፡ይብሉ፡ደሙ፡ላዕሌነ፡ወላዕለ፡ውሉድነ፡ይኩን።

፳፪፤ ወእምዝ፡ይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡እስቅሎኑ፡ለንጉሥክሙ፡ወእምዝ፡አውሥኡ፡ወይቤልዎ፡አልብነ፡ንጉሥ፡ዘእንበለ፡ቄሳር፡ስቅሎ።እስመ፡ኵሉ፡ዘያነግሥ፡ርእሰ፡ዐላዊ፡ነጋሢ

የሆሣዕና፡ዋዜማ።

፲፫፤ ይልቁንም፡በእነዚህ፡በስድስቱ፡ቀኖች፡መጾም፡የሚችል፡ቢኖር፡ሁለት፡ሁለት፡ቀን፡ይጹም፤የማይችል፡ግን፡አንድ፡አንድ፡ቀን፡ይጹም፤ከክፉም፡ሥራ፡ሁሉ፡ይጠበቅ።

፲፬፤ ጌታችን፡ሙሽራው፡ከእነርሱ፡ጋር፡ሳለ፡የሙሽራው፡ሚዜዎች፡መጾም፡አይችሉም።ነገር፡ግን፡ሙሽራውን፡ከእነርሱ፡ለይተው፡የሚወስዱበት፡ወራት፡ይመጣል፤ያን፡ጊዜ፡ይጾማሉ፡ብሏልና።

፲፭፤ በእነዚህም፡በስድስት፡ቀናት፡ውስጥ፡አይሁድ፡ከእኛ፡ወስደው፡በእንጨት፡ላይ፡ሰቅለውታልና፡ከበደለኞች፡ጋራም፡ቈጥረውታልና።

፲፮፤ ስለዚህም፡ጌታችን፡ወደ፡ሰማያት፡ካረገ፡በኋላ፡እኛ፡እንዳደረግነው፡ትጾሙ፡ዘንድ፡እናዝዛችኋለን።

፲፯፤ ሌሎችንም፡ቀኖች፡እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ይጹሙ፤እጨምራለሁ፡የሚል፡ግን፡ፀሐይ፡እስኪገባ፡ድረስ፡ይጹም።

፲፰፤ በቤተ፡ክርስቲያንም፡ውስጥ፡ተሰብስባችሁ፡አሪትንና፡መጻሕፍተ፡ነቢያትን፡የዳዊትንም፡መዝሙር፡እያነበባችሁ፡በምስጋናና፡በጸሎት፡ዶሮ፡እስከሚጮህ፡ድረስ፡የሌሊቱን፡ሰዓት፡ጠብቁ።

፲፱፤ የሚጠመቁትንም፡ካጠመቃችኋቸው፡በኋላ፡በመፍራትና፡በመንቀጥቀጥ፡ሁናችሁ፡የዳዊትን፡መዝሙር፡አንብቡ፤ለሕዝቡም፡ለነፍሳቸው፡የሚጠቅማቸውን፡አስተምሩአቸው።

፳፤ እስራኤል፡ወደ፡ንስሓ፡ተመልሰው፡ከክህደት፡ይድኑ፡ዘንድ፡እግዚአብሔርን፡ለምኑት፤ፈራጁ፡ጲላጦስ፡እጁን፡ታጥቦ፡ከዚህ፡ከጻድቅ፡ሰው፡ደም፡እኔ፡ንጹሕ፡ነኝ፡ብሏልና።

፳፩፤ እስራኤል፡ግን፡ደሙ፡በእኛና፡በልጆቻችን፡ላይ፡ይሁን፡እያሉ፡ጮኹ።

፳፪፤ ከዚህም፡በኋላ፡ጲላጦስ፡ንጉሣችሁን፡ልስቀለውን? አላቸው።እነሱም፡መልሰው፡ከቄሳር፡በቀር፡ንጉሥ፡የለንም።ስቀለው፡

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፭፫፤ ወአውሥኡ ፡ ወይቤልዎ ፡ እመ ፡ አሕየውኮ ፡ ለዝንቱ፡ኢኮንክ፡ዐርኮ፡ለቄሳር።	፭፫፤ እነሱም፡ይህንን፡ካዳንከው፡የቄሳር፡ወዳጁ፡ አይደለህም፡ብለው፡መለሱለት።
፭፬፤ ጲላጦስ ፡ መኰንን ፡ ወሄሮድስ ፡ ንጉሥ ፡ አዘዙ፡ይስሕልዎ።	፭፬፤ ገዢው ፡ ጲላጦስና ፡ ንጉሡ ፡ ሄሮድስ ፡ ይሰቅሉት፡ዘንድ፡አዘዙ።
፭፭፤ ከመ ፡ይትፈጸም ፡ዘይቤ ፡ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ። ወሕዝብኒ ፡ነበቡ ፡ከንቶ።	፭፭፤ አሕዛብ ፡ለምን ፡ ተሰበሰቡ? ሕዝቡስ ፡ ለምን ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ተናገሩ?
፭፮፤ ወተንሥኡ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር። ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ። ላዕለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወላዕለ መሲሑ።	፭፮፤ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ በጠላትነት ፡ ለምን ፡ ተነሡ። አለቆችም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በመሢሑ ላይ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ፡ያለው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ነው።
፭፯፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ወገደፉ ፡ እጎሃሆሙ ፡ ከመ ፡ በድን ፡ርኩስ።	፭፯፤ ዳግመኛም ፡ ወንድማቸውን ፡ እንደረከሰ ፡ በድን ፡ ጣሉ ፡ አለ።
፭፰፤ ወእምዝ ፡ ሰቀልዎ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ወተንሥአ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት።	፭፰፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ሰቀሉት ። በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ እሑድ ፡ ተነሣ።
፭፱፤ ወተፈጸመ ፡ ዘይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወኰንና ፡ ለምድር ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ትወርስ ፡ በኵሉ ፡ አሕዛብ።	፭፱፤ መጽሐፍ ፡– አቤቱ ፡ ተነሥ ! ምድርንም ፡ ፍረድባት። አንተ ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሠል ጥነህባቸው ፡ ትኖራለህና ፡ ያለው ፡ ተፈጸመ።
፮፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ይእዜ ፡ እትነሣእ ፡ ይቤ ፡ እግዚ አብሔር ። እሬሲ ፡ መድኃኒተ ፡ ወአግሀድ ፡ ቦቱ።	፮፤ ዳግመኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ሦስት ፡ መዐልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በክርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሬ ፡ እነሣለሁ ፡ አለ ። ድኅነትን ፡ አደር ጋለሁ ፡ በእርሱም ፡ እገልጣለሁ ፡ አለ።
፯፩፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ በመዓትከ ፡ ወተለዓል ፡ መልዕልቶሙ ፡ ለጸላዕትየ።	፯፩፤ ሁለተኛም ፡ አቤቱ ፡ በቍጣህ ፡ ተነሣ። በጠ ላቶቼ ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በል ፡ አለ።
፯፪፤ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ፍድዮሙ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ላዕለ ፡ ርእሶሙ።	፯፪፤ ደግሞም ፡ ፍዳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ አምጣ ባቸው ፡ አለ።
፯፫፤ ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ አንትሙ ፡ አብኡ ፡ ቍርባ ኀከሙ ፡ በከመ ፡ አዘዘከሙ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ግበሩ ፡ ተዝካርየ።	፯፫፤ ስለዚህ ፡ እንደአዘዛችሁ ፡ መሥዋዕታችሁን ፡ አቅርቡ ፡ አለ ፤ እንደዚህ ፡ መታሰቢያዬን ፡ አድርጉ ፡ ብሏልና።
፯፬፤ ጹሙኬ ፡ ጾመ ፡ ሠናየ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበሐሜት ፡ ወግበሩ ፡ በዓለ ፡ እስመ ፡ ተንሥአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እሙታን ፡ ዘአሰፈወነ ፡ ትንሣኤሁ።	፯፬፤ በፍጹም ፡ ደስታ ፡ መልካም ፡ ጾምን ፡ ጹሙ ፤ በዓልንም ፡ አድርጉ። መነሣቱን ፡ ተስፋ ፡ ያስደ ረገን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሥቷልና።
፯፭፤ ዛቲ ፡ ሥርዓት ፡ ትኩንክሙ ፡ ሕገ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ እስከ ፡ ይመጽእ ፡ ዳግመ ፡ በስብሐት። እምቀኖና ፡ አቡሊዲስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዘ ፡ ሐዋርያት።	፯፭፤ ይህችም ፡ ሥርዓት ፡ ዳግመኛ ፡ በጌትነት ፡ እስከ ሚመጣ ፡ ድረስ ፡ ለዘላለሙ ፡ ሕግ ፡ ትሁናችሁ። የሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊዲስ ፡ ከሠራው ፡ ሥርዓት ፡ የተገኘች ፡ እርሷም ፡ የሐዋርያት ፡ ትእዛዝ ፡ ናት።
በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ቀኖና ፡ ዘዕሥራ ፡ ወክልኤቱ።	በሥርዓት ፡ መጽሐፍ ፡ በሃያ ፡ ሁለተኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደተጻፈ።
፭፤ ይቤ ፡ በሰሙን ፡ ዘይደሉ ፡ ለፍሥሐ ፡ አይሁድ ፡ ለይትዐቀቡ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ በዐቢይ ፡	፭፤ የአይሁድ ፡ ፋሲካ ፡ በሚሆንበት ፡ በሕማማት ፡ ሰሞን ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ መጠበቅ ፡

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
ተዐቅቦ፡ወይጸሙ፡ባቲ፡እምኵሉ፡ፍትወት፡እስከ ፡ቃለ ፡ኢይትናገሩ ፡በፍሥሓ ፡አላ ፡በሐዘን።	ይጠበቁ፡ከፈቃደ ፡ሥጋ ፡ሁሉ ፡ይጹሙባት፡የሐዘንን ፡እንጂ ፡የደስታን ፡ቃል ፡እስከ ፡አለ መናገር፡ድረስ።
፱፤ ወተአምሩ ፡ከመ ፡እግዚአ ፡ኵሉ ፡ዘኢየ ሐምም፡ሐመ ፡በእንቲአነ ፡ባቲ ፡ከመ ፡ንትዐገሥ ፡ሕማማተ ፡ወነሥአ ፡ሕማመ ፡ዘድልው፡ለነ፡በእንተ፡አበሳነ።	፱፤ የማይታመም፡የሁሉ፡ጌታ፡ስለእኛ፡መከራ፡እን ደተቀበለባት፡እኛም፡መከራውን ፡እንታገሥ፤ ዘንድ ስለ ፡በደላችን ፡ለእኛ ፡መሆን፡የሚገባ ውንም፡መከራ፡እንደተቀበለ፡ታውቃላችሁ።
፲፤ ወንሕነ ፡ካዕበ ፡ንሳተፍ ፡ሕማማተ ፡ዘተወክፈ፡በእንቲአነ ፡ከመ ፡ንሳተፎ ፡ካዕበ ፡በውስተ፡መንግሥቱ።	፲፤ ዳግመኛም ፡ስለ ፡እኛ ፡የተቀበለውን ፡መከራ፡በመቀበል ፡አንድ ፡እንሁን ፤ ሁለተኛ ፡በሰማ ያዊት ፡መንግሥቱ ፡አንድ ፡እንሆን ፡ዘንድ።
፲፩፤ ወመብልዕሰ ፡ዘይደሉ ፡በዛቲ ፡ሰሙን ፡ጎብስት፡ወጼው፡ውማይ፡ባሕቲቱ።	፲፩፤ በዚችም ፡በሕማማት ፡ሰሞን ፡የሚገባ ፡ምግብ፡እንጀራ፡ጨውና፡ውሃ፡ብቻ፡ነው።
፲፪፤ ወለእመ ፡ኮነ ፡አሐዱ ፡ድውየ ፡አው ፡በሀገር ፡ዘአልቦ ፡ውስቴታ ፡ክርስቲያን ፡ወተፈጸመ ፡እንከ ፡ጊዜ ፡ሕማማት ፡እንዘ ፡ኢየአምር ፡አው፡በውስተ፡ደዌሁ።	፲፪፤ አንድ ፡ምእመን ፡የታመመ ፡ቢሆን ፡ወይም ፡ክርስቲያን ፡በሌለበት ፡አገር ፡ሁኖ ፡ሳያውቅ ፡የሕማማት ፡ሰሞን ፡ቢያልፍ ፡ወይም ፡በደዌ ፡ውስጥ ፡ሁኖ ፡ቢቀርበት።
፲፫፤ ይጹም ፡እምድኅረ ፡በዓለ ፡ኀምሳ ፡ወይግበር ፡ፍሥሓ ፡በጸማ ፡ወይጠይቅ ፡ውሳጥያቲሁ ፡ከመ፡ኢይትኀየል ፡በኢፈሪሀ።	፲፫፤ ከበዓለ ፡ሐምሳ ፡በኋላ ፡ሰውነቱን ፡በማድ ከም ፡ደስታን ፡ያድርግ ፤ ባለመፍራት ፡እንዳ ይጠፋ ፡ውስጣዊ ፡ሰውነቱን ፡ይመርምር።
፲፬፤ ወኢይጹም ፡ባሕቲቶ ፡ከመ ፡ኢይግበር ፡መሠረተ ፡ካልአ ፡እምዘተሠርዐ። ወኢያፍልስ ፡ዘንተ ፡ሰብእ ፡በአእምሮ ፡አላ ፡ይግበር ፡ዋሕደ።	፲፬፤ ከተሠራው ፡ሥርዓት ፡ሌላ ፡መሠረት ፡እንዳያ ደርግ ፡ይኸንኑ ፡ብቻ ፡አይጹም ። በማወቅ ፡ሰው ፡ይህንን ፡አያፋልስ ፤ አንድ ፤ ጊዜ ፡ብቻ ፡ያድርግ ፡እንጂ።
፲፭፤ ወኢይግበር ፡መሠረተ ፡ካልአ ፡ለእመ ፡ከልአ ፡ደዌ ፡አው ፡በኢያእምሮ። ወካዕበ ፡ይቤ ፡በቀኖና ፡ዘሠላሳ ፡ወሰመንቱ።	፲፭፤ በሽታው ፡ከልክሎት ፡ወይም ፡ሳያውቅ ፡ቢቀርበት ፡ሌላ ፡መሠረት ፡አይመሥርት። ዳግመኛም ፡በሠላሳ ፡ስምንተኛው ፡የቀኖና ፡አንቀጽ ፡ተናገረ።
፲፮፤ ትኩን ፡ሌሊተ ፡ትንሣኤሁ ፡ቅድስት ፡ለእግ ዚእነ ፡በተዐቅቦ ፡ዐቢይ ፡ወኢይኑም ፡መኑሂ ፡ፍጹመ ፡እስከ ፡ነግህ።	፲፮፤ የጌታችን ፡የከበረች ፡የትንሣኤው ፡ሌሊት ፡በታላቅ ፡ጥንቃቄ ፡ትሁን ፡እስከሚነጋ ፡ድረስም ፡ማንም ፡ፈጽሞ ፡አይተኛ።
፲፯፤ ወካዕበ ፡ይጎዕቡ ፡ሥጋሆሙ ፡በማይ ፡እምቅድመ ፡ይፍትሑ ፡ጸመ ፡ወይኩኑ ፡ኵሉ ፡ሕዝብ ፡ያጎትዉ።	፲፯፤ ሁለተኛም ፡ጾምን ፡ከመፍታታቸው ፡በፊት ፡ገላቸውን ፡በውሀ ፡ይታጠቡ ፡ሕዝቡም ፡ሁሉ ፡መብራትን ፡የሚያበሩ ፡ይኹኑ።
፲፰፤ እስመ ፡በይእቲ ፡ሰዓት ፡ረሰየ ፡መድኅን ፡አግዓዝያነ ፡ኵሎ ፡ዓለመ።	፲፰፤ በዚያች ፡ሰዓት ፡መድኃኒታችን ፡ዓለሙን ፡ሁሉ ፡ነፃ ፡አድርጎአልና።
፲፱፤ ወአምለክዎ ፡ሰማያውያን ፡ወምድራውያን ፡ወኵሉ ፡ዘውስቴታ ፡እስመ ፡ውእቱ ፡ተንሥአ ፡እሙታን ፡ወዐርገ ፡ውስተ ፡ሰማያት ፡ወነበረ ፡በየማነ ፡አብ።	፲፱፤ ሰማያውያንና ፡ምድራውያን ፡በውስጧ ፡ያሉትም ፡ሁሉ ፡አመለኩት ፤ እርሱ ፡ከሙታን ፡ተለይቶ ፡ተነሥቶ ፡ወደ ፡ሰማያትም ፡ወጥቶ ፡በአብ ፡ቀኝ ፡ተቀምጧልና።
፳፤ ወካዕበ ፡ይመጽእ ፡በስብሐተ ፡አቡሁ ፡ወመላእክቲሁ ፡ምስሌሁ ፡ይኰንን ፡ኵሎ ፡ዓለመ ፡ለለ ፡አሐዱ ፡አሐዱ ፡በከመ ፡ምግባሩ።	፳፤ ዳግመኛም ፡ለእያንዳንዱ ፡እንደየሥራው ፡በመክፈል ፡በዓለሙ ፡ሁሉ ፡ይፈርድ ፡ዘንድ ፡በአባቱ ፡ጌትነት ፡ከመላእክቱ ፡ጋር ፡ይመጣል።
፳፩፤ ዘገብረ ፡ሠናየ ፡ኀበ ፡ትንሣኤ ፡ሕይወት ፡ወዘገብረ ፡እኩየ ፡ውስተ ፡ትንሣኤ ፡ዘለደይን ፡በከመ ፡ጽሑፍ። ወበእንተዝ ፡ይደልወነ ፡ንኩን ፡ንቁሃነ ፡ኵሎ ፡ጊዜ ፡ወኢነሀብ ፡ንዋመ ፡ለአዕይንቲነ ፡ወኢድቃሰ ፡ለቀራንብቲነ ፡እስከ ፡ንረክብ ፡መካኖ ፡ለእግዚአብሔር።	፳፩፤ በጎ ፡የሠራ ፡የሕይወት ፡ትንሣኤን ፡ክፉ ፡የሠራ ፡የፍርድ ፡ትንሣኤን ፡ይነሣል ፡ተብሎ ፡እንደተጻፈ። ስለዚህም ፡ሁልጊዜ ፡ነቅተን ፡መኖር ፡ይገባናል። የእግዚአብሔርንም ፡የጸጋውን ፡ቦታ ፡እስከምናገኝ ፡ድረስ ፡ለዐይኖቻችን ፡እንቅልፍን ፡ለሽፋሽፍቶቻችን ፡ሽልብታን ፡እንስጥ።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
እምቀኖና፡ሐዋርያት፡ትእዛዝ፡አርብዓ።	ከሐዋርያት፡ቀኖና፡አርባኛ፡ትእዛዝ።
፩፤ ኢይደሉ፡ለመኑሂ፡እምእመናን፡በክርስቶስ፡ ይጥዐም፡ወኢምንተኒ፡በሰሙነ፡ሕማማት፡ እምቅድመ፡ጊዜ፡ዘይደሉ፡ይብልዑ፡ባቲ።	፩፤ ይበሉባት ፡ዘንድ ፡ከተወሰነችው ፡ጊዜ ፡በፊት፡በሕማማት ፡ሰሞን ፡ምንም ፡ምን ፡ይቀምሱ ፡ዘንድ ፡በክርስቶስ ፡ከአመኑ ፡ምዕመናን፡ወገን፡ለማንም፡አይገባም።
፪፤ አላ፡ለእመ፡ኮነ፡ድውየ፡ዘኢይክል፡ይጹም፡ ክልኤተ፡ዕለተ። ለይጹም፡ዕለተ፡ሰንበት፡ በእንተ፡ትካዝ፡ወይትከላእ፡ወኢይጥዐም፡ ኅብስተ፡ወጼወ።	፪፤ ሁለት፡ቀን፡መጾም፡የማይችል፡በሽተኛ፡ ቢሆን ፡ግን ፡ቀዳም ፡ሥዑርን ፡ይጹም ፡የሐዘን፡ቀን፡ስለሆነች፡እንጀራና፡ጨውም፡ አይቅመስ።
፫፤ ወለእመ፡ኮነ፡ብእሲ፡ዘኢየአምር፡ሰሙነ፡ ሕማማት ፡ለይጹም ፡እምድኅረ ፡በዓለ ፡ኅምሳ። ወአኮ፡ውእቱ፡ሰሙነ፡ሕማማት፡ ከመ፡ይዕቀብ፡አላ፡አምሳል፡ወይደሉ፡ከመ፡ ይጹም፡ህየንቴሁ።	፫፤ ሰሙነ፡ሕማማትን ፡ያላወቀ ፡ሰው ፡ቢኖር ፡ከበዓለ ፡ኅምሳ ፡በኋላ ፡ይጹም ። እርሱ ፡የሕማማት ፡ሰሞንን ፡እንዲጠብቅ ፡አይደለም። ለምሳሌው ፡ነው ፡እንጂ ፡በእርሱም፡ፈንታ፡ይጾም፡ዘንድ፡ይገባል።
፬፤ ተፈጸመ፡ቀኖና፡ዘይደሉ፡ለሰሙነ፡ሕማማት፡ ቅዱስ፡ዘይደሉ፡ያንብቡ፡ዘንተ፡ዲበ፡ሕዝብ፡ ሠርከ፡ሰንበት፡ዘሆሣዕና፡እሁድ።	፬፤ ለከበረ ፡ለሕማማት ፡ሰሞን ፡ለሕዝቡ ፡ያነቡት፡ዘንድ ፡የሚገባው ፡ሥርዓት ፡ተፈጸመ፤ ይኸም፡ከሆሣዕና፡እሁድ፡ዋዜማ፡ እስከ፡ቀዳሚት፡ሰንበት፡ማታ፡ነው።
፭፤ ያብጽሐነ ፡እግዚአብሔር ፡ጎቤሃ ፡ለዝሉን ፡ምስለ፡በግዕ፡ዘበአማን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወልደ ፡እግዚአብሔር ፡ሕያው ፡ውስተ ፡መንግሥቱ ፡በከመ ፡አሰፈወ ፡ወይቤ ፡አንትሙ፡ ትነብሩ ፡ምስሌየ ፡በውስተ ፡ማዕድየ።	፭፤ እናንተ ፡ከእኔ ፡ጋራ ፡በማዕዴ ፡ትቀመጣላችሁ፡ብሎ ፡ተስፋ ፡እንደሰጠን ፡ከእውነተኛው፡በግ፡ከሕያው፡እግዚአብሔር፡ልጅ፡ ከኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጋራ፡ወደ፡እርሷ፡ወደ፡ መንግሥቱ ፡ሁላችንን ፡እግዚአብሔር ፡ያድርሰን።
፮፤ ወይረሲ፡አሚነ፡ወሰላመ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያኑ፡ርትዕት፡አርቶዶክሳዊት፡ፍጡነ።	፮፤ በቀናች ፡(ትክክል) ፡በሆነች ፡በአርቶዶክስ ፡ተዋሕዶ ፡ቤተክርስቲያኑ ፡ሰላምንና ፡አንድነትን፡ፈጥኖ፡ያድርግልን።
፯፤ ወያጽንዕ ፡ሕዝቦ ፡ወመርዔቶ ፡ኅሩየ ፡ላዕለ ፡ሃይማኖት ፡በስሙ ፡ወበጎይለ ፡መስቀሉ ፡ንጹሕ፡ከመ፡ያድኅን፡ዅሎ፡ዓለመ፡ውሉደ፡ ጥምቀት፡እምእደ፡ሰብእ፡እኩያን።	፯፤ ሕዝቡንና፡የተመረጠ፡መንጋውን፡በስሙ፡በሃይማኖትና፡ንጹሕ፡በሆነ፡በመስቀሉ፡ኃይል፡ ያጽና ፡ከክፉዎች ፡ሰዎች ፡እጅ ፡ዓለምን፡ ሁሉና፡የተጠመቁትን፡ሰዎች፡ያድን።
፰፤ እስመ ፡ሎቱ ፡ስብሐት ፡ወክብር ፡ወእዘዝ ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።	፰፤ ምስጋና ፡ክብር ፡ኃይል ፡ጽንዕ ፡ለእርሱ ፡ነውና፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፩፤ በስመ ፡ሥሉስ ፡ቅዱስ ፡ዕሩይ ፡አሐዱ ፡አምላክ፡ ሥላሴ ፡በአሐዱ ፡ልዑል ፡ላዕለ ፡ዅሉ።	፩፤ ልዩ፡ሦስት፡ትክክል፡በሚሆን፡ከሁሉ፡በላይ፡ ልዑል፡በሆነ፡ሦስትነት፡በአንድነት፡አንድነት፡ በሦስትነት፡በአለው፡በአንድ፡አምላክ፡ስም።
፪፤ ሠራየ ፡ኃጢአት ፡ለዅሉ ፡ዘውእቱ ፡አምላከሙ፡ለክርስቲያን።	፪፤ ለሁሉ ፡ኀጢአትን ፡የሚያስተሠርይ ፡ይኸውም፡የክርስቲያኖች፡አምላክ፡ነው።
፫፤ ወሶበ ፡ኮነ ፡ቀኖና ፡ሐዋርያት ፡ይኤዝዝ ፡አንብቦ ፡ብሉይ ፡ወሐዲስ ፡በሰሙነ ፡ሕማማት፡ዘእግዚእነ፡ወመድኃኒነ።	፫፤ እንዲህም ፡ሆነ ፡የሐዋርያት ፡ሥርዓት ፡በጌታችን ፡በመድኃኒታችን ፡በሕማሙ ፡ሰሞን፡ብሉይንና፡ሐዲስን፡ማንበብን፡ያዛል።
፬፤ ኮነ ፡ዝንቱ ፡ጥዩቀ ፡ወንቡረ ፡ለዅሉ ፡እስከ ፡ነበረ፡አቡነ ፡አባ ፡ቅብርያል ፡ወልደ ፡ታሪክ ፡ሊቀ ፡ጳጳሳት ፡ዘላዕለ ፡መንበረ ፡ማርቆስ ፡ወንጌላዊ፡ወሐዋርያ፡ዘውእቱ፡ኮነ፡ጸሐፌ።	፬፤ ይኸም ፡ጸሐፊ ፡የነበረው ፡የታሪክ ፡ልጅ ፡አባታችን ፡አባ ፡ቅብርያል ፡በወንጌላዊውና ፡በሐዋርያው ፡በማርቆስ ፡ወንበር ፡ሊቀ ፡ጳጳሳት፡እስከ፡ተቀመጠ፡ድረስ፡ይህ፡ለሁሉ፡ የኅላና፡የተረዳ፡ነገር፡ሆነ።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፩፤ ወርእየ ፡ ሰብአ ፡ በምግባራቲሆሙ ፡ ወቅኔ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳንንት ፡ ወመሳፍንት ፡ ወዘተርፈ ፡ ምግባራተ ፤ ወኢክህሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ቀኖና፡ሐዋርያት።	፩፤ ሰዎችን ፡ በሥራቸው ፡ የነገሥታቱን ፡ የመኳንንቱንና ፡ የመሳፍንቱን ፡ ግዛት ፡ የቀረውንም ፡ ሥራ ፡ አየ ፡ የሐዋርያትንም ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸም ፡ አልቻሉም።
፪፤ ወቦ ፡ እማእምራን ፡ ወለባውያን ፡ ወጠቢባን ፡ መነኮሳት ፡ ብዙኃን ፡ እምደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ነሥኡ ፡ እምብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ወገብሩ ፡ መጽሐፈ ፡ ወሰመይዎ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕማማት።	፪፤ ከአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ ከአዋቂዎች ፡ መካከል ፡ አስተዋዮችና ፡ ብልሆች ፡ መነኮሳት ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ወስደው ፡ መጽሐፍን ፡ አዘጋጁ ፡ ይህንንም ፡ መጽሐፈ ፡ ሕማማት ፡ ብለው ፡ ሰየሙት።
፫፤ ወኮኑ ፡ ይገብሩ ፡ ቦቱ ፡ ፍሥሓ ፡ በበ ፡ ዅሉ ፡ ዓመት ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ ዅሉ ፡ ዘዚአሁ ፡ አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘተሠይመ ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ብሕንሳ ፡ ነጸረ ፡ ዘንተ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ ከመ ፡ ገብሩ ፡ ውስተ ፡ ሰዓት ፡ ደኅሪ ፡ ኢገብሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ወንጌል ፡ ባሕቲቱ ፤ ወአንከረ ፡ በዝንቱ ፡ ጥቀ።	፫፤ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በየዓመቱ ፡ ዅሉ ፡ የሕማማትን ፡ ሥርዓት ፡ ያደርጉ ፡ ነበር። ዅሉ ፡ የእርሱ ፡ የኾነው ፡ በብሕንሳ ፡ ተሹሞ ፡ የነበረ ፡ አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እስከነበረ ፡ ድረስ ፡ እርሱም ፡ ይኸን ፡ የግብረ ፡ ሕማማትን ፡ መጽሐፍ ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ እንደሠሩ ፡ ተመለከተ ፡ ይኸውም ፡ ከብፇው ፡ ከወንጌል ፡ በስተቀር ፡ በዚህም ፡ እጅግ ፡ አደነቀ።
፬፤ ወነሥአ ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪት ፡ ወነቢያት ፡ ወመጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ወመጽሐፈ ፡ ሰሎሞን ፡ ንጉሥ። ወረሰየ ፡ ውስተ ፡ ዅሉ ፡ ሰዓት ፡ ዘይደሉ ፡ ባቲ ፡ እስከ ፡ ኮኑ ፡ ዅሉሙ ፡ ዕሩያ።	፬፤ ከኦሪት ፡ ከነቢያት ፡ ከነዌ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ ከንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ መጽሐፍ ፡ ወስዶ ፡ ሁላቸው ፡ ትክክል ፡ እስከ ፡ ሆኑ ፡ ድረስ ፡ በየሰዓቱ ፡ ሁሉ ፡ የሚገባውን ፡ አደረገ።
፭፤ ወረሰየ ፡ በዅሉ ፡ ዕለት ፡ ክልኤተ ፡ ምዕዳን ፡ እምነገረ ፡ አበው ፡ አሐዱ ፡ በነግህ ፡ ወአሐዱ ፡ በሠርክ።	፭፤ አባቶች ፡ ከተናገሩት ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ተግሣፅና ፡ ምክር ፡ በየቀኑ ፡ አንዱ ፡ በነግህ ፡ አንዱ ፡ በማታ ፡ እንዲነበብ ፡ አደረገ።
፮፤ ወንሕነ ፡ ንስአሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይሥረይ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ወአበሳነ ፡ ወየሀበነ ፡ ሞገሰ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእ ፡ አሜን።	፮፤ እኛም ፡ በደላችንንና ፡ ኀጢአታችንን ፡ ያስተሠርይልን ፡ ዘንድ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ሆነ ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ በእውነት ፡ ባለሟልነትን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምነው። አሜን።
፯፤ ወእግዚእ ፡ ይፈጽም ፡ ለነ ፡ በሰላም ፡ ለዅልነ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ አሜን። ቃል ፡ ዘተብህለ ፡ እምኅበ ፡ ክቡር ፡ ስምዖን ፡ ዐምዳዊ ፡ ዘይትነበብ ፡ በማኅትወ ፡ ሰንበት ፡ ዘሆሣዕና።	፯፤ ጌታም ፡ ለሁላችን ፡ ለክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ የቸርነቱን ፡ ሥራ ፡ ይፈጽምልን። አሜን። በሆሣዕና ፡ ሰንበት ፡ ዋዜማ ፡ የሚነበብ ፡ ከከበረ ፡ ከስምዖን ፡ ዐምዳዊ ፡ የተነገረ ፡ ቃል።
፰፤ ኦ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመጻእከ ፡ በትሕትና ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዘ ፡ ትጼአን ፡ ላዕለ ፡ እድግት ፡ ከመ ፡ ትሑት።	፰፤ እንደ ፡ ተዋረደ ፡ ሰው ፡ በአህያ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በትሕትና ፡ የመጣህ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ።
፱፤ ኦ ፡ ዘትነብር ፡ ዲበ ፡ አክናፈ ፡ ኪሩቤል ፡ ወሠረገላተ ፡ እሳት ፡ ያሌዕሉ ፡ ለከ ፡ ስብሐተ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ኅቡአቲከ።	፱፤ በእሳት ፡ ሠረገላዎችና ፡ በኪሩቤል ፡ ክንፎች ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ ሆይ ፡ በማይመረመረው ፡ ቦታህ ፡ ውስጥ ፡ ምስጋናን ፡ ለአንተ ፡ ያቀርባሉ።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፩፤ እስመ፡አንተ፡ኢትትዌሰን፡እንዘ፡ሰማያት፡ወምድር፡ምሉአን፡እምስብሐቲከ።	፩፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ከጌትነትህ ፡ የተነሣ ፡ የተመሉ፡ሲሆኑ፡አንተ፡አትወሰንምና።
፪፤ አእላፈ ፡ አእላፋት ፡ ዘይሰግዱ ፡ ቅድመ ፡ ዕበይከ፡ መጻእከ ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በትሕትና።	፪፤ የብዙ፡ብዙ፡የሆኑ፡አእላፋት፡መላእክት፡በኀ ናናነትህ ፡ ፊት ፡ የሚሰግዱልህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩ ሳሌም፡በትሕትና፡መጣህ።
፫፤ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሀበኒ ፡ መንፈሰ ፡ ትሕትና ፡ ዘይወልድ ፡ ኵሎ ፡ ትሩፋት፡በውስተ፡ነፍስ፡ወዘይመልእ፡ኵሎ፡ ሥነ፡ፍሥሓ።	፫፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በሰውነት፡ ውስጥ ፡ ትሩፋትን ፡ ሁሉ ፡ የሚወልደውንና ፡ ተድላ ፡ ነፍስን ፡ ሁሉ ፡ ምሉዕ ፡ የሚያደር ገውን፡የትሕትና፡መንፈስን፡ስጠኝ።
፬፤ ወአድኅነኒ፡እመንፈሰ፡ትዕቢት፡ዘይወልድ፡ ኵሎ፡ሕማማተ፡ብዙኃተ፡ወያበውእ፡ነፍሰ፡ ውስተ፡ጣቃ፡ጽልመት።	፬፤ ብዙ፡መከራዎችን፡ከሚወልድና፡ነፍስንም፡ ወደድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ከሚያስገባ ፡ ከትዕቢት፡መንፈስ፡አድነኝ።
፭፤ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ረስየኒ ፡ ምስለ፡ አርዳኢከ ፡ ከመ ፡ እፃእ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፤ ወአእትት ፡ እምላዕሌየ ፡ ወምላኅ ፡ ፍቅሮ፡ እምልብየ ፡ እፀመድ ፡ ወእትአሰር ፡ በአርዑተ፡ትእዛዝከ።	፭፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም፡ እለይ ፡ ዘንድ ፡ ፍቅሩንም ፡ ከልቡናየ ፡ ነቅለህ ፡ ታስወግደውና ፡ በትእዛዝህም ፡ ቀንበር፡ ተጠምጂ ፡ እታሰር ፡ ዘንድ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርትህ፡ጋር፡አድርገኝ።
፮፤ ወረስዮ፡ይጽላእ፡ዘንተ፡ዓለመ፡ወኵሎ፡ፍት ወታቲሁ፡ወይትአሰር፡በአፍቅሮትከ።	፮፤ ልቡናዬ ፡ ይኸን ፡ ዓለምና ፡ ፍላጎቱን ፡ ሁሉ ፡ ይጠላ ፡ ዘንድ ፡ በፍቅርህም ፡ ይታሰር ፡ ዘንድ ፡ አድርገው።
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ፡አምላክ፡ዘለዓለም፡ሥላሴ።	አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ የዘለዓለም ፡ ሦስትነት ፡ በአለው ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም።
፩፤ ስቡሕ ፡ ወውዱስ ፡ ዘኅረረ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ በአሐቲ፡ቃል።	፩፤ በአንዲት ፡ ቃል ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ ፈጽሞ፡የተመሰገነ።
፪፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት፡ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ፡ስብሐቲከ፡ዘሀሎ፡ወይሄሉ።	፪፤ ልዩ፡ከቡር፡ጽኑዕ፡አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡የጌ ትነትህ፡ምስጋና፡በሰማይና፡በምድር፡የመላ፡ አስቀድሞ፡የነበረና፡ወደፊትም፡የሚኖር፡ነው።
፫፤ አ፡እግዚአ፡መሐረነ፡አ፡እግዚአ፡ባርከነ፡አ፡ እግዚአ፡ተሣሀለነ፡አሜን።	፫፤ አቤቱ ፡ ማረን ፡ አቤቱ ፡ አክብረን ፡ አቤቱ ፡ ይቅር፡በለን፤አሜን።
፬፤ ሃሌ፡ሉያ፡ለአብ፡ሃሌ፡ሉያ፡ለወልድ፡ሃሌ፡ ሉያ፡ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ስብሐት ፡ ለወልድ ፡ ስብሐት ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ።	፬፤ ለአብ ፡ ምስጋና ፡ ለወልድ ፡ ምስጋና ፡ ለመንፈስ፡ቅዱስ ፡ምስጋና፡ይገባል፤ ለአብ፡ ምስጋና ፡ ለወልድ ፡ ምስጋና ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ምስጋና፡ይገባል።
፭፤ ንስግድ፡ለአብ፡ንስግድ፡ለወልድ፡ንስግድ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።	፭፤ ለአብ ፡ እንስገድ ፡ ለወልድ ፡ እንስገድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንስገድ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፮፤ ወረስየን ፡ እግዚአ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ንበልከ ፡ በአኰቴት።	፮፤ አቤቱ ፡ በምሥጋና ፡ እንጠራህ ፡ ዘንድ ፡ የተዘ ጋጀን፡አድርገን።
፯፤ አቡነ፡ዘበሰማያት፡ይትቀደስ፡ስምከ።	፯፤ አባታችን ፡ ሆይ ፡ በሰማያት ፡ የምትኖር ፡ ስምህ፡ይመስገን።

ዘግሥትወ፡ሦላዕና።	የሦላዕና፡ዋዜማ።
፩፡ ትምጻእ፡መንግሥትከ።	፩፡ መንግሥትህ፡ትምጣ።
፪፡ ወይኩን፡ፈቃድከ። በከመ፡በሰማይ፡ከማሁ፡በምድር።	፪፡ ፈቃድህ ፡ በሰማይ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሁ ፡ በምድር፡ይሁን።
፫፡ ሲሳየነ፡ዘለለ፡ዕለትነ፡ሀበነ፡ዮም።	፫፡ የዕለት፡ምግባችንን፡ዛሬ፡ስጠን።
፬፩፡ ኀድግ፡ለነ፡አበሳነ፡ወጌጋየነ፡ከመ፡ንሕነኒ፡ንኀድግ፡ለዘአበሰ፡ለነ።	፬፩፡ እኛም፡የበደለንን፡ይቅር፡እንድንል፡በደላች ንንና፡ኃጢአታችንን፡ይቅር፡በለን።
፭፩፡ ኢታብአነ፡እግዚኦ፡ውስተ፡መንሱት። አላ፡አድኅነነ፡ወባልሐነ፡እምኵሉ፡እኩይ።	፭፩፡ አቤቱ፡ ወደ፡ፈተና፡አታግባን፡ከክፉ፡ሁሉ፡አድነን፡እንጂ።
፮፩፡ እስመ ፡ ዚአከ ፡ ይእቲ ፡ መንግሥት ፡ ኃይል ፡ ወስብሐት፡ለዓለመ፡ዓለም።	፮፩፡ ይህቺ ፡ መንግሥት ፡ ከኀሊነትና ፡ ጌትነት ፡ ለዘላለሙ፡ፀንዘቦችህ፡ናቸውና።
፩፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በግዕ ፡ ዘበአማን ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ግበር ፡ ምስሌነ፡ምሕረተ፡በመንግሥትከ።	፩፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እውነተኛ ፡ በግ ፡ በመንግሥትህ ከእኛ፡ጋር፡ምሕረትን፡አድርግ።
፪፡ እስመ ፡ አፈ ፡ አቡከ ፡ ይከውን ፡ ስምዐ ፡ ለከ ፡ እንዘ፡ይብል ፡ አንተ ፡ ወልድየ ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ።	፪፡ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ ዛሬም ፡ ወለድኩህ ፡ ሲል ፡ አባትህ፡ለአንተ፡ምስክር፡ሁኖሃልና።
፫፡ ኪሩቤልኒ ፡ ይቀውሙ ፡ ታሕቴከ ፡ ወሱራፌልኒ፡ኢይኔጽሩከ።	፫፡ ኪሩቤል ፡ ከበታችህ ፡ ይቆማሉ ፡ ሱራፌልም ፡ አያዩህም።
፬፡ ወንሕነሰ ፡ ንሬእየከ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ በውስተ ፡ ምሥዋዕ፡ቅዱስ።	፬፡ እኛ ፡ ግን ፡ በቅዱስ ፡ መሠዊያ ፡ ውስጥ ፡ ሁልጊዜ፡እናይሃለን።
፭፡ ወንነሥእ፡ሥጋከ፡ወደመከ፡ክቡረ።	፭፡ የከበረ፡ሥጋህንና፡ደምህንም፡ እንቀበላለን።
፮፡ ወኵሉ ፡ ስባሔ ፡ መንፈሳዊ ፡ ይደሉ ፡ ለከ ፡ አ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፮፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምስጋና፡ሁሉ፡ለአንተ፡ይገባል።
፯፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዕብን ፡ ዘበአማን ፡ ዘኢይትዐወቅ ፡ ሤጡ ፡ ዘወሀበ ፡ ነጋዲ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ወተሣየጦ።	፯፡ ዋጋው፡የማይታወቅ፡ነጋዴ፡ገንዘቡን፡ሁሉ፡ሰጥቶ ፡ የተወዳጀው ፡ እውነተኛ ፡ ዕንቁ ፡ ደንጊያ፡አንተ፡ነህ።
፰፡ ግበር ፡ ለነኒ ፡ ዓዲ ፡ ይእዜ ፡ ዘንተ ፡ እብነ ፡ ያብርህ፡ላዕሌነ፡በብእሲነ፡ዘውስጥ።	፰፡ ይህንን ፡ የዕንቁ ፡ ደንጊያ ፡ በሰውነታችን ፡ ውስጥ፡ያበራ፡ዘንድ፡ደግሞ፡ዛሬ፡ለእኛ፡አድርግልን።
፱፡ ሥርጋዌ ፡ ነፍስነ ፡ ወትፍሥሕተ ፡ ልብነ ፡ ውእቱ፡ስምከ፡ቅዱስ፡አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፱፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ የተቀደሰው፡ ስምህ ፡ የልባችን ፡ ደስታ ፡ የሰውነታችን፡ሽልማት፡ጌጥ፡ነው።
፲፡ ኪሩቤል ፡ ይጠፍሁ ፡ በክነፊሆሙ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ወይቄድስዎ ፡ ለእግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።	፲፡ ኪሩቤል ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ ፈጽመው፡ያመሰግኑታል።
፲፩፡ አ ፡ ርኅሩኅ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ አበ ፡ ኵሉ፡ምሕረት።	፲፩፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ የምሕረት ፡ ሁሉ ፡ አባት፡ርኅሩኅ፡ሆይ።
፲፪፡ የዐርብ ፡ ፀሐይ ፡ በጊዜሁ ፡ ወአንተሰ ፡ አንተ ፡ ክመ፡ወዓመቲከኒ፡ዘኢየኀልቅ።	፲፪፡ ፀሐይ፡በጊዜው፡ጊዜ፡ይጠልቃል፡አንተ፡ግን፡ መቼም ፡ መች ፡ ያው ፡ ነህ ፤ ዘመንህም ፡ አይፈጸምም።
፲፫፡ እስመ ፡ በአስተሐምሞ ፡ ሂሩትከ ፡ አጽንንከ ፡	፲፫፡ ቸርነትህንም ፡ በማከናወን ፡ ልዑል ፡ ባሕር

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
ስማያተ ፡ ወወረድከ ፡ ኃቤነ ፡ ከመ ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ጠቢብ ፡ ዘበአማን ፡ መፈውስ ፡ ፈወስከ፡ኵሎ፡ደዌነ።	ይህን ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ ወደእኛ ፡ ወርደህ ፡ እውነተኛ፡ አዳኝ ፡ እንደሆነ ፡ ብልህ ፡ ዓቃቤ ፡ ሥራይ፡ደዌያችንን፡ሁሉ፡አዳንህ።
፲፩፤ ነጽር ፡ ኅቤየ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡በዐይነ፡ሣህልከ፡እንተ፡ዘኒሩትከ።	፲፩፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የባሕርይ፡ቸርነትህ፡ በምትሆን፡በይቅርታህ፡ዓይን፡ወደእኔ፡ተመልከት።
፲፪፤ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስድድ ፡ እምኔየ ፡ ኵሎ ፡ መንፈስ ፡ እኪይ ፡ እንተ ፡ ዘጸላኢ፡ ወረሲ ፡ ውስቴትነ ፡ ኅሊና ፡ ንጹሐ ፡ ከመ፡ንዘክርከ።	፲፪፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ከጠላት ፡ የሆነው ፡ ክፉ ፡ መንፈስን ፡ ሁሉ ፡ ከእኔ ፡ አርቅልኝ ፤ አንተን ፡ እናስብህ ፡ ዘንድ ፡ በውስጣችን፡ንጹሕ፡ልቡና፡አድርግልን።
፲፫፤ ያድኩ ፡ ምድረ ፡ ወኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ኢረክብኩ ፡ እግዚኦ ፡ ስመ ፡ ጥዑመ ፡ ዘእንበለ ፡ ስመ ፡ እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፲፫፤ አቤቱ ፡ ምድርንና ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ዞርኹ ፤ ያለ፡ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ ጣፋጭ ፡ስምን ፡ አላገኘሁም።
፲፬፤ ወኵሉ ፡ ረድኤት ፡ ወኵሉ ፡ ኃይል ፡ ዘዲበ ፡ ምድር፡ኢይከውን ፡ዘእንበለ ፡ እመንገለ ፡ ስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።	፲፬፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ረድኤትና ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ያለጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ አይሆንም።
፲፭፤ ኵሉ ፡ ዘመደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እለ ፡ አሥመርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እመንገለ ፡ ስመ፡እግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ ፡ውእቱ።	፲፭፤ እግዚአብሔርን ፡ ያገለገሉ ፡ የሰው ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ በኩል ፡ ነው።
፲፱፤ ወኵሉ ፡ አምሃ ፡ ክቡረ ፡ ወጎሩየ ፡ ኢነሣእነ ፡ ዘእንበለ ፡ በስመ ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ።	፲፱፤ የከበረና ፡ የተመረጠውን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ ፡ስም ፡ አልተቀበልንም።
፳፤ ሰማይኒ ፡ ወምድርኒ ፡ ኢጸንኡ ፡ እንበለ ፡ ሁከት ፡ ዘእንበለ ፡ በስመ ፡እግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ።	፳፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያለጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከሁከት ፡ አልጸኑም።
፳፩፤ ወስድስቱ ፡ ማየ ፡ መሳብክት ፡ ኢኮነ ፡ ወይነ ፡ ጎሩየ ፡ ዘእንበለ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።	፳፩፤ የስድስቱ ፡ ጋኖች ፡ ውኃ ፡ ያለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ የተመረጠ ፡ ወይን ፡ አልሆነም።
፳፪፤ ወኃይላት ፡ ዐበይት ፡ ወሊቃን ፡ መላእክት ፡ ይሴብሕዎ ፡ ወይባርክዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፳፪፤ ታላላቆች ፡ ኃይላትና ፡ የመላእክት ፡ አለቆች ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፈጽመው ፡ ያመሰግኑታል።
፳፫፤ ሰማኒቱ ፡ ነፍስ ፡ ድኅኑ ፡ እማየ ፡ አይኅ ፡ እመንገለ ፡ ስመ ፡እግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ።	፳፫፤ ስምንቱ ፡ ነፍሳት ፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ የዳኑት ፡ በጌታችን ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ ፡ስም ፡ በኩል ፡ነው።
፳፬፤ ሐራ ፡ ሰማይ ፡ ወነገሥተ ፡ ምድርኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለከ።	፳፬፤ የሰማይ ፡ ሠራዊትና ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ይገዙልሃል።
፳፭፤ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተሰፋ ፡ መሲሓውያን ፡ ኵሉ ፡ ነፍስ ፡ ያመልኩከ ፡ ወይባርኩከ።	፳፭፤ የክርስቲያኖች ፡ ተስፋና ፡ አለኝታ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ክርስቶስ ፡ሆይ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ያመልኩሃል ፡ ያመሰግኑሃልም።
፳፮፤ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ አርቶዶክሳዊ ፡ ኅቡረ ፡ ይሴብሕ ፡ ወይባርክ ፡ለእግዚአብሔር።	፳፮፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ የአርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ እግዚአብሔርነትህን ፡ ፈጽሞ ፡ ያመሰግናል።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፳፯፤ ስመ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እግዚእየ፡ይጥዕም፡ እምጸቃውዐ፡መዓር፡ወሦከር።	፳፯፤ የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ከማር፡ ወለላና፡ከሦከር፡ይጥማል።
፳፰፤ እስመ፡መዓርሰ፡ወሦከር፡ሶበ፡ይበልዑ፡ እምኔሆሙ፡ይጸገቡ፡ወስመ፡እግዚእየ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኢይጸገብ።	፳፰፤ ማርና፡ሦከር፡በሚበሉበት፡ጊዜ፡ይጠገባሉ፡ የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ግን፡አይ ጠገብም።
፳፱፤ ከናፍርየ፡ያንጠበጥባ፡መዓረ፡ሶበ፡እቤ፡ ስመ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፳፱፤ የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ስም፡በምጠራ፡ ጊዜ፡ከንፈሮቼ፡ማርን፡ያንጠባጥባሉ።
፴፤ እስመ፡ለመዓር፡ወለሦከር፡ወለመና፡ አልቦሙ፡ጣዕም፡በኀቤየ፡እምስመ፡ እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፴፤ ማር፡ስኳርና፡እንጀራ፡ቢሆኑም፤እንደ፡ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡በኔ፡ዘንድ፡ ጣዕም፡የላቸውም።
፴፩፤ እስመ፡ስመ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ይኄይሰኒ፡ወይኄይስ፡እምኵሉ፡ፍጡር፡ ዘታሕተ፡ሰማይ።	፴፩፤ የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ይሻለ ኛልና፡ከሰማይ፡በታች፡ካለ፡ፍጥረት፡ ሁሉም፡ይበልጣልና።
፴፪፤ ርኅራኄከ፡ብዙኅ፡ወኢይትነገር፡አ፡እግዚእየ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዕዉቅ፡ውእቱ፡ስምከ፡ ውስተ፡አፈ፡ኵሉ፡ዘየአምን፡ብከ፡ወያፈቅረከ።	፴፪፤ ቸርነትህ፡ብዙ፡ነው።አይነገርምም፤ጌታዬ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በሚያምንብህና፡ በሚወድህ፡አፍ፡ሁሉ፡ስምህ፡የታወቀ፡ነው።
፴፫፤ ኵሉ፡ስባሔ፡ዘሕግ፡አልቦ፡ውስቴቶሙ፡ዘይ ትማሰለከ።	፴፫፤ በሕግ፡ከታወቁ፡ምስጋናዎች፡ሁሉ፡ከውስ ጣቸው፡የሚመስልህ፡የለም።
፴፬፤ ብርሃነ፡አዕይንትየኒ፡ወኃይለ፡ሥጋየኒ፡ እምስምከ፡ቅዱስ፡ውእቱ።	፴፬፤ የዓይኖቼ፡ብርሃንና፡የሥጋየ፡ብርታት፡ ከከበረው፡ስምህ፡ወገን፡ነው።
፴፭፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ረሲ፡ ስመከ፡ቅዱሰ፡ሥዩመ፡ዘልፈ፡ውስተ፡አፉየ፡ እስከ፡ተፍጻሜተ፡ሕይወትየ።	፴፭፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡እስከ፡ ሕይወቴ፡መጨረሻ፡የከበረ፡ስምህን፡በአን ደበቴ፡ዘወትር፡የተሾመ፡አድርገው።
፴፮፤ ኵሉ፡ነፍሰ፡ክርስቲያን፡አርቶዶክሳውያን፡ ኅቡረ፡ይባርኩ፡ወይሴብሑ፡ስመ፡እግዚእየ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፴፮፤ የኦሮቶዶክስ፡ተዋሕዶ፡ክርስቲያን፡ ሰውነት፡ሁሉ፡የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ ስም፡በአንድነት፡ያከብራሉ፤ያመሰግናሉ።
፴፯፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አሰስል፡ እምኔየ፡ኵሎ፡መናፍስተ፡እከይ፡እንተ፡ ዘኅጢአት።	፴፯፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ከኃጢአት፡ ወገን፡የሚሆን፡የክፋት፡መንፈስን፡ሁሉ፡ ከእኔ፡አስወግድ።
፴፰፤ ተፈሥሑ፡ወተመክሑ፡ኵልክሙ፡መሲሓ ውያን፡በዝንቱ፡ስም፡መድኃኒነ፡ዘእግዚእየ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፴፰፤ መዳኛችን፡በሚሆን፡በዚህ፡በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ክርስቲያኖች፡ ሁላችሁም፡ፈጽሞ፡ደስ፡ይበላችሁ።
፴፱፤ ጥዑም፡ውእቱ፡ስመ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ወይጥዕም፡እምፍሬ፡ገነት።	፴፱፤ የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ጣፋጭ፡ነው፡ በገነት፡ካለ፡ፍሬም፡ይልቅ፡ይጣፍጣል።
፵፤ ወበመዝሙር፡ቅዱስ፡እንተ፡አቡነ፡ዳዊት፡ ንሴብሕ፡ወንዜምር፡ወንቁድስ፡ስመ፡ እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፵፤ አባታችን፡ዳዊት፡በአመሰገነበት፡በከበረ፡ መዝሙር፡የጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ ስም፡ፈጽሞ፡እናመሰግናለን፡እናከብራለን።
፵፩፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከዐው፡ ላዕሌየ፡ጸጋ፡ዐቢየ፡እንተ፡ዘመንፈስ፡ቅዱስ።	፵፩፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ብዙ፡የሆነ፡ የመንፈስ፡ቅዱስን፡ጸጋ፡በኔ፡ላይ፡አሳድር።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፸፪፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስድድ፡እምኔየ፡ኵሎ፡መንፈሰ፡ዘኢያሠምረከ፡እስእል፡ወአኀሥሥ፡እምኀቤከ።	፸፪፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡አንተን፡ደስ፡የማያሰኝህን፡ሐሳብ፡ሁሉ፡ከእኔ፡ታርቅ፡ዘንድ፡ወዳንተ፡እለምናለሁ፡ከአንተም፡እሻለሁ።
፸፫፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ግበር፡ምስሌየ፡ምሕረተ፡በመንግሥትከ።	፸፫፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በጌትነትህ፡ከእኔ፡ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ።
፸፬፤ ንሰግድ ፡ ለከ ፡ አ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፤ ንሰግድ ፡ ለከ ፡ አ ፡ አምላክነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፤ ንሰግድ ፡ ለከ ፡ አ ፡ መድኀኒነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ አቡከ ፡ ኄር ፡ ሰማያዊ ፡ ወመንፈስከ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ።	፸፬፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ እንሰግድልሃለን፤ ፈጣሪያችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ እንሰግድልሃለን ፤ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ፡ ሰማያዊ ፡ ከሚሆን ፡ ከቸር ፡ አባትህ ፡ ጋራ ማሕየዊ ፡ ከሚሆን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ጋራ፡እንሰግድልሃለን።
፸፭፤ በከመ፡ሰገደ፡ለከ፡ዐቢይ፡ዐምደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡አባ፡አቡሊዲስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡በውስተ ፡ ድርሳኑ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ነአምን ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ሠለስቱ፡ገጻት፡ፍጹማን፡መልክእ፡ወአካል፡እሙንቱ፡እንዘ፡አሐዱ፡መለኮቶሙ።	፸፭፤ የሮሜ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የቤተ፡ክርስቲያን፡ምሰሶ፡የሆነ፡ታላቁ፡አባት፡አቡሊዲስ፡በድርሳኑ፡ባሕርያቸው፡በእውነት፡አንድ፡ሲሆን፡በመልክ፡በአካል ፡ ፍጹማን ፡ የሚሆኑ ፡ ሦስት ፡ ገጻት ፡ እንደሆኑ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናምናለን፡ብሎ፡እንደሰገደልህ።
፸፮፤ ዘበአማን፡አሐደ፡ስግደተ፡ይሰገዱ፡ወአሐደ፡ስብሐተ፡ይሰብሑ።	፸፮፤ በእውነት ፡ አንድ ፡ ስግደት ፡ ይሰገድላቸዋል ፡ አንድ ፡ ምስጋናም ፡ ይመሰገናሉ።
፸፯፤ ወበዝንቱ፡አእመርነ፡ከመ፡አሐዱ፡ውእቱ፡መለኮተ፡ሥላሴ፡ወሎቱ፡ንሰግድ።	፸፯፤ በዚህም ፡ የሥላሴ ፡ መለኮታቸው ፡ አንድ ፡ እንደሆነ፡አወቅን፤ለእርሱም፡እንሰግዳለን።
፸፰፤ እለሰ ፡ ይብሉ ፡ አሐዱ ፡ እግዚእ ፡ ወካልኡ ፡ ገብር ፡ ረሲዓን ፡ እሙንቱ ፡ ለእመ ፡ ሰገዱ ፡ ለዘ ይብልዎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ገብር ፡ አው ፡ ኢሰገዱ፡ ለዘተሣየጠነ ፡ በደሙ ፡ እስመ ፡ የአምኑ፡በክልኤቱ፡ህላዌ።	፸፰፤ አንዱ ፡ ገዥ ፡ አንዱ ፡ ተገዥ ፡ የሚሉ ፡ ግን ፡ መናፍቃን ፡ ናቸው ። ተገገርም ፡ እንደሆነ ፡ ለሚናገሩለት ፡ ከሰገዱ ፡ ወይም ፡ በወርቀ ፡ ደሙ ፡ ለዋጀን ፡ ካልሰገዱ ፡ በሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አምነዋልና።
፸፱፤ ወያጌብሮሙ ፡ ይስግዱ ፡ ለአሐዱ ፡ ወለካልኡ ፡ ኢይስግዱ።	፸፱፤ ይህም ፡ ለአንዱ ፡ እንዲሰግዱ ፡ ለሁለተኛው ፡ እንዳይሰግዱ ፡ ያስገድዳቸዋል።
፹፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ረሰዩ ፡ ስመ ፡ መለኮት ፡ ኀበ ፡ ግብርናት፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ ክቡር ፡ ጳውሎስ ፡ ወልድኒ ፡ ይገኒ ፡ ለዘአግነየ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎ።	፹፤ ክቡር ፡ ጳውሎስም ፡ ወልድ ፡ ሁሉን ፡ ለአስገዛለት ፡ ይገዛል ፡ ስላለ ፡ የመለኮትን ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ተገዥ ፡ ሥጋ ፡ የለወጡ ፡ አሉ።
፹፩፤ ንሕነኒ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰገደ ፡ ለአብ፡ በሥጋ።	፹፩፤ እኛስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለአብ ፡ በሥጋ ፡ እንደሰገደ ፡ እናምናለን።
፹፪ ለሊሁኒ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ንሰግድ ፡ ለዘ ነአምር ፡ አንትሙሰ ፡ ትሰግዱ ፡ ለዘኢተ አምሩ።	፹፪፤ እርሱም ፡ ራሱ ፡ እኛስ ፡ ለምናውቀው ፡ እንሰግዳለን፤እናንተ፡ግን፡ለማታውቁት፡ትሰግዳላችሁ፡ብሏል።
፹፫፤ ባህቱ ፡ ኢተፈልጠ ፡ መለኮት ፡ እምትስብእት ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ይሰግድ ፡ ለአብ ፡ በሥጋ ። ወሥጋሂ፡ ኢተፈልጠ ፡ ሶበ ፡ ይሰግድ ፡መለኮት። ወኢተአተተ ፡መለኮት ፡ ሶበ ፡ ይሰግድ ፡ ትስብእት። ወኢይደሉ ፡ ይኩን ፡ ግሙራ፡ገዝኑቱ።	፹፫፤ ነገር ፡ ግን ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ለአብ ፡ ሲሰግድ ፡ መለኮት ፡ ከሥጋ ፡ አልተለየም ። መለኮትም ፡ በሰገደ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋ ፡ አልተለየም ፤ ሥጋም ፡ ሲሰግድ ፡ መለኮት ፡ አልተለየም ። መለኮት ፡ ከትስብእት ፤ ትስብእት ፡ ከመለኮት ፡ ሊለይ ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባም።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፶፬፤ ዘሰ፡ይብል፡ከመ፡ሥጋ፡አምላክ፡ውእቱ፡ወይሰግድ፡ሎቱ፡በተዋሕዶ፡እንበለ፡ፍልጠት፡እስመ፡ሥጋሁ፡ለቃል፡ዘኢተፈጥረ፡ብፁዕ፡ውእቱ፡እስመ፡ኢተዐቅፈ፡በሥጋሁ፡ወኢበሕማማቲሁ።	፶፬፤ ሥጋ፡አምላክ፡እንደሆነና፡የቃል፡ሥጋ፡ያልተፈጠረ፡ነው፡ብሎ፡ያለመለየት፡በተዋሕዶ፡የሚሰግድለት፡ግን፡ብፁዕ፡ነው። በሥጋውና፡በመከራው፡አልተጠራጠረምና።
፶፭፤ ወንሰግድ፡ሎቱ፡ምስለ፡ሥጋሁ፡አሐተ፡ስግደተ።	፶፭፤ ከሥጋው፡ጋር፡አንዲት፡ስግደትን፡እንሰግድ ለታለን።
፶፮፤ ወካዕበ፡ይብል፡ዝንቱ፡መምህር፡እመቦ፡ዘሰገደ፡ለቃል፡ናሁ፡ሰገደ፡ለሥጋ፡ዘሂ፡ሰገደ፡ለሥጋ፡ናሁ፡ሰገደ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል።	፶፮፤ ዳግመኛም፡ይህ፡መምህር፡እንዲህ፡አለ፡ለቃል፡የሰገደ፡ቢኖር፡ለሥጋ፡ሰገደ፡ለሥጋም፡የሰገደ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል፡ሰገደ።
፶፯፤ ወከማሁ፡ዓዲ፡አበዊነ፡ሐዋርያት፡ሶበ፡ሰገዱ፡ለሥጋ፡ቅዱስ፡ሰገዱ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል።	፶፯፤ ዳግመኛም፡እንዲሁ፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡ለከበረ ሥጋ፡በሰገዱ፡ጊዜ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል፡ሰገዱ።
፶፰፤ ወከማሁ፡መላእክትሂ፡ኮኑ፡ይትለአኩ፡ለአርአያ፡ሥጋ፡ወየአምሩ፡ከመ፡ውእቱ፡እግዚአመ፡ወሎቱ፡ይሰግዱ።	፶፰፤ መላእክትም፡እንዲሁ፡አካል፡ሥጋን፡ያገሰግሉ፡ነበር፤ ጌታችውም፡እንደሆነ፡አውቀው፡ይሰግዱለታል።
፶፱፤ ረሲዕሰ፡ረሰዮ፡ለእግዚእ፡ከመ፡አሐዱ፡እምአግብርት፡ወያሰትት፡ስግደተ፡ለመድኅን።	፶፱፤ ዝንጉ፡ተጠራጣሪ፡ግን፡ጌታን፡ከፍጡራን፡እንደ፡አንዱ፡አድርጎ፡ለመድኀን፡ስግደት፡አይገባውም፡አለ።
፷፤ ንሕነሰ፡ንሰግድ፡ለክርስቶስ፡ከመ፡ውእቱ፡አምላክ፡እስመ፡ኵሉ፡ብርክ፡ይሰግድ፡ሎቱ፡እለ፡በሰማይ፡ወእለ፡ውስተ፡ምድር።	፷፤ እኛ፡ግን፡አምላክ፡እንደሆነ፡አምነን፡ለክርስቶስ፡እንሰግዳለን፤ ጉልበት፡ሁሉ፡በሰማይም፡በምድርም፡ውስጥ፡ያለ፡ፍጥረት፡ሁሉ፡ይሰግድለታልና።
፷፩፤ ወካዕበ፡ይብል፡ዝንቱ፡አብ፡እመቦ፡ዘይፈልጦ፡ለመድኅን፡በእንተ፡ትስብእቱ፡ወሕማማቲሁ። ወይሰግድ፡ለብእሲ፡ህየንተ፡እግዚአብሔር፡ወይብል፡እስመ፡ዘተሰቅለ፡ብእሲ፡ዕሩቅ፡እመለኮት፡ወያፈልስ፡መለኮተ፡ለከዊነ፡ትስብዕት፡ዘእግዚአብሔር፡ዘኮነ፡በትስብዕት፡ውእቱ፡ኢይረክብ፡መድኀኒተ፡እስመ፡ብእሲ፡ዕሩቅ፡እመለኮት፡ኢይክል፡ያድኅን፡ዓለመ።	፷፩፤ ሁለተኛም፡ይህ፡አባት፡እንዲህ፡አለ፡ሰው፡ስለመሆኑና፡መከራ፡ስለመቀበሉ፡መድኀንን፡የሚከፍለው፡ለእግዚአብሔር፡በመስገድ፡ፈንታ፡ለዕሩቅ፡ብእሲ፡የሚሰግድ፡የተሰቀለውንም፡ከመለኮት፡የተለየ፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ነው፡የሚል፡መለኮትንም፡ሥጋ፡ወደ፡መሆን፡የሚለውጥ፡ቢኖር፡እግዚአብሔር፡ሰው፡በመሆኑ፡ያደረገለትን፡ድኅነት፡ኢያገኝም። ከመለኮት፡የተለየ፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ዓለምን፡ያድን፡ዘንድ፡አይችልምና።
፷፪፤ ወሞቱ፡ለብእሲ፡ዕሩቅ፡ኢያነጽሐ፡ለዘይጠመቅ፡በስሙ።	፷፪፤ የዕሩቅ፡ብእሲ፡ሞትም፡በስሙ፡የሚጠመቀውን፡ሊያነጻው፡አይችልምና።
፷፫፤ ወካዕበ፡ይብል፡ቅዱስ፡ወክቡር፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘቍስጥንጥንያ፡በውስተ፡ድርሳኑ፡እንዘ፡ይተረጕም፡ቃለ፡መልእክቱ፡ለብፁዕ፡ጳውሎስ፡ጎበ፡ዕብራውያን።	፷፫፤ ዳግመኛም፡የቍስጥንጥንያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ቅዱስና፡ክቡር፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡የተመሰገነ፡ጳውሎስ፡ወደ፡ዕብራውያን፡የጻፈውን፡መልእክት፡በድርሳኑ፡ሲተረጕም፡እንዲህ፡አለ።
፷፬፤ ቦኑ፡ሱታፌ፡ዘይፈደፍድ፡እምዝንቱ፡ከመ፡ይሣእ፡ሥጋ፡እምህላዌነ፡ዘይነብር፡በየማነ፡	፷፬፤ ከእኛ፡የነሣውን፡ሥጋ፡በእግዚአብሔር፡ቀኝ፡(በዕሪና)፡የሚቀመጥ፡መልእክትም፡የሚለን፡

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
እግዚአብሔር ፡ ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ መላ እክት።	ዱለት፡ከመሆን፡በውኑ፡ከዚህ፡የሚበልጥ፡ አንድነት፡አለን?
፷፭፤ ለዝንቱሰ፡ሶበ፡እዜከሮ፡ብዙኀተ፡ጊዜያተ፡ አነክር ፡ ወእዴመም ፡ እስመ ፡ መንክር ፡ ፈድፋደ ፡ ልዕልና ፡ ሥጋ ፡ እንተ ፡ ነሥአ ፡ እምኔነ፡አስገዶሙ፡ለመላእክት፡ወለሊቃነ፡ መላእክት።	፷፭፤ ይህንን ፡ ባሰብኩት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እደነቃለሁ ፤ እገረማለሁ ፡ ከእኛ ፡ የነሣው ፡ የሥጋ ፡ ልዕልና ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነውና ፡ መላእክትንና፡የመላእክት፡አለቆችንም፡አሰ ገዳቸው።
፷፮፤ ወካዕበ፡ይብል፡ብሩህ፡ማኅቶት፡ቤተ፡ክርስ ቲያን ፡ አባ ፡ ኢራቅሊስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘኪስኪስ፡እንዘ፡ሀሎ፡ውስተ፡ሕዕነ፡እሙ፡ ያንሶሱ ፡ በክነፈ ፡ ነፋስ ፡ ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ መላእክት።	፷፮፤ ዳግመኛም ፡ ብሩህና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መብራት ፡ የኪስኪስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ኢራቅሊስ ፡ በእናቱ ፡ ክንድ ፡ ሳለ ፡ በነፋስ ፡ ክንፍ፡ይመላለስ፡ነበር። መላእክትም፡ይሰግ ዱለት፡ነበር፡አለ።
፷፯፤ ወካዕበ፡ይብል፡ዝንቱ፡ሥሙር፡ኤጲስቆጶስ፡ አሐዱ፡ህላዌ፡ወአሐዱ፡አካል፡ውእቱ፡እግ ዚአብሔር፡ቃል፡ዘኮነ፡ሥጋ።	፷፯፤ ዳግመኛም ፡ ይህ ፡ ተወዳጅ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሰው፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡ነው፡አለ።
፷፰፤ ወንሰብክ ፡ ዘንተ ፡ ገሀደ ፡ ወንሰግድ ፡ ሎቱ ፡ ምስለ፡ሥጋሁ፡አሐተ፡ስግደተ።	፷፰፤ ይሽንንም፡በግልጽ፡እናስተምራለን፤ከሥጋውም፡ ጋራ፡አንዲት፡ስግደትን፡እንሰግድለታለን።
፷፱፤ ወእመቦ ፡ ዘኢየአምን ፡ ከመዝ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን።	፷፱፤ እንደዚህ ፡ የማያምን ፡ ቢኖር ፡ የተለየ ፡ ይሁን።
ተግሣጽ።	ተግሣጽ።
፩፤ አ፡አይሁዳዊ፡ኅድግ፡ስሕተተከ፡እምዝንቱ፡ ወስግድ፡ለዘተሰቅለ።	፩፤ አይሁዳዊ፡ሆይ፡ከዚህ፡የተነሣ፡ይህን፡ስሕተ ትህን፡ተው፤ለተሰቀለውም፡ስገድ።
፪፤ ወጽራሕ፡ምስለ፡ሙሴ፡ነቢይ፡እንዘ፡ትብል፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ አምላኪየ ፡ እሴብሖ ፡ አምላከ ፡ አቡየ፡ወአሌዕሎ።	፪፤ ይህ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነው ፡ አመሰግነዋለሁ ፤ ይህ ፡ የአባቴ፡ፈጣሪ፡ነው፤ከፍ፡ከፍ፡አደርገዋለሁ፡ እያልክ፡ከነቢዩ፡ከሙሴ፡ጋራ፡አመስግን።
፫፤ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወዕዘዝ ፡ ወስግደት ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ኄር ፡ ሰማያዊ ፡ ወመንፈሱ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ ። ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።	፫፤ ለእርሱ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ጽንዕ ፡ ስግደት ፡ ሰማያዊ፡ከሚሆን፡ከቸር፡አባቱ፡ጋር፤አዳኝ፡ ከሚሆን ፡ ከቅዱስ ፡ መንፈሱ ፡ ጋር ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም፡ለዘለዓለሙ፡ይሁን፡አሜን።
ተግሣጽ፡ዘዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ።	የዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡ተግሣፅና፡ምክር።
በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።	በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር ፡ አሜን።
፩፤ አ ፡ ፍቁራንየ ፡ ንጉየይ ፡ እምፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ወሥሥዕት ፡ ወእምፈቲወ ፡ ንዋየ ፡ ዓለም።	፩፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ገንዘብ ፡ ከመውደድና ፡ ከሥሥት ፡ በዓለም ፡ ያለውንም ፡ ሀብት ፡ ከመመኘት፡እንራቅ።
፪፤ እስመ ፡ ዘሕሙም ፡ በዝንቱ ፡ ደዌ ፡ ይፈቱ ፡ ያዝንም ፡ ሰማይ ፡ ወርቀ ፡ ወታፍሪ ፡ ምድር ፡ መሳብክተ ፡ ብሩር ፡ ወታንቅዕ ፡ ፈልፈለ ፡	፪፤ በዚህ ፡ በፍቅረ ፡ ነዋይ ፡ ደዌ ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ ሰማይ ፡ ወርቅን ፡ ያዘንምለት ፡ ዘንድ ፡ ምድርም ፡ የብር ፡ ጋኖችን ፡ ታፈራለት ፡

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
ጳዝዮን፡ወይትወለጡ፡አድባር፡ወርቀ።	ዘንድ፡ጳዝዮን፡የተባለውንም፡ጥሩ፡ዕንቁ፡ታመነጭለት፡ዘንድ፡ተራሮችም፡ወደ፡ወርቅ፡ይለወጡ፡ዘንድ፡ይወዳል።
፫፤ ይጸልእ፡ክቡራን፡ከመ፡ያስተጋብእ፡ንዋዮሙ።	፫፤ ገንዘባቸውን፡ይሰበስብ፡ዘንድ፡ባለጸጎችን፡ይጠላል።
፬፤ ወይጸልእ፡ምስኪናን፡ወይፈርህ፡ከመ፡የሀቦሙ።	፬፤ ይሰጣቸው፡ዘንድ፡ይፈራልና፡ጦም፡አዳሪዎችንም፡ይጠላል።
፭፤ ወይክሕድ፡አኀወ፡ወአዝማደ፡ወፍቁራኑ፡ወሕዝበ።	፭፤ ወንድሞችንና፡ዘመዶችን፡ወዳጆችንና፡ወገኖችንም፡ይክዳል።
፮፤ ወጥቡዕ፡ለዙኔ፡ዐበይት፡ወይነውኅ፡ተርጕሞታ።	፮፤ በታላላቆች፡ላይ፡ለመፍረድ፡ጨካኝ፡ነው፡ትርጓሜዋም፡እጅግ፡ይረዝማል።
፯፤ ወለእመ፡ኮነ፡ይሁዳ፡ዘተሰምየ፡ረድአ፡ወሐዋርያ፡ወስምዐ፡ኮነ፡ላእለ፡መንክራተ፡ክርስቶስ።	፯፤ ደቀ፡መዝሙርና፡ሐዋርያ፡የተባለ፡ይሁዳ፡ክርስቶስ፡ባደረጋቸው፡አስደናቂ፡ተአምራት፡ላይ፡ምስክር፡ቢሆንም።
፰፤ ወሶበ፡ረከቦ፡ፍቅረ፡ንዋይ፡መሠጦ፡ዝንቱ፡ደዌ፡ልቡናሁ፡ወኮነ፡ኅሡአ፡ልቡና፡ወጽሉመ፡ንጸሬ፡ወፍጥረተ፡አርዌ፡ሰይጣናዊ፡ሙሱን፡ኅሊና፡ኅሙመ፡ራእይ፡ወዕሩቅ፡እምላብሰ፡ሃይማኖት፡ወውሁጥ፡ውስተ፡ባሕረ፡ኅጢአት፤ ወመስተኅልቅ፡ላዕለ፡ሜጠ፡እግዚኡ፡ወኅሉቍ፡ምስለ፡ሰይጣናት።	፰፤ ፍቅረ፡ንዋይ፡ባደረበት፡ጊዜ፡ይህ፡የገንዘብ፡መውደድ፡በሽታ፡ልቡን፡ማረከው።አእምሮውን ያጣ፡ዐይነ፡ልቡናው፡የጨለመ፡ሰይጣናዊ፡ፍጥረተ፡አርዌ፡ልቡ፡የጠፋ፡መልኩ፡የከፋ፡ከሃይማኖት፡ልብስ፡የተራቆተ፡በኅጢአት፡ባሕር፡የሰጠመ፡ጌታውን፡ለመሸጥ፡የቆረጠ፡ከሰይጣናት፡ጋራ፡የተቈጠረ፡ሆነ።
፱፤ ወዛቲ፡ብእሲት፡ዘአጽንዐት፡ልባ፡ሶበ፡ገደፈት፡ንዋያ፡ደለዋ፡ትግሥሥ፡እማረ፡እግዚእነ፡ወታርሕስ፡በአንብዓ፡ወመዝመዘቶ፡በሥዕርተ፡ርእሳ፡ከመ፡ትንሣእ፡ሥርየተ፡ኅጢአታ፡ብዙኅ፡ወተጸገወት፡ተድላ፡ወሞገሰ።	፱፤ ይህች፡ልቧን፡ያበረታች፡ሴት፡ገንዘቧን፡በተወች፡ጊዜ፡የጊታችንን፡እግሩን፡ትዳስስ፡ዘንድ፡በዕንባዋም፡ታርሰው፡ዘንድ፡ተገባት፤ የብዙ፡ኃጢአቷንም፡ሥርየት፡ትቀበል፡ዘንድ፡በራስዋ፡ወጉርም፡አሸችው፤ ተድላ፡ደስታንና፡ባለሟልነትንም፡ተቀበለች።
፲፤ ወሶበ፡አእመርን፡ይእዜኒ፡በእንተ፡ድቀቱ፡ለይሁዳ፡ወላዕለ፡ዛቲ፡ዘማ፡ንትጋደል፡ወንጽናዕ፡በዘንርኅቅ፡እምፍቅረ፡ንዋይ።	፲፤ አሁንም፡ስለ፡ይሁዳ፡መውደቅና፡በዚህች፡በአመንዝራይቱ፡ላይ፡የሆነውን፡ጸጋ፡ክብር፡ካወቅን፡ከፍቅረ፡ንዋይ፡በምንርቅ፡ገንዘብ፡ጸንተን፡ተጋድሎ፡እናድርግ።
፲፩፤ ወንጕየይ፡እምኩይ፡ወኢንቅድም፡ኅበ፡ሥጋኪግዚእ፡ከመ፡ይሁዳ።	፲፩፤ ከክፉ፡ሥራም፡እንራቅ፤ እንደ፡ይሁዳም፡ሁኔን፡ወደጌታ፡ሥጋ፡አንቅረብ
፲፪፤ ወንሕነ፡እጎዛን፡በፍቅረ፡ንዋይ፡ከሡት፡በክልኤ፡ገጽ፡ወንጌሊ፡ቂመ፡ወቅንአት፡ወሥሥዕተ፡ከርሥ፡ወጸገ፡ወትዕግልተ፡ወዕልወተ፡ወንረክብ፡ቦቱ፡ኵነኔያተ፡ወዐቢየ፡ደይነ።	፲፪፤ እኛም፡በሁለት፡ወገን፡በፍቅረ፡ንዋይ፡ተይዘናል፤ ቅናትና፡ቂምን፡ለሆድ፡መላሳትን፡ክፋትን፤ ቅሚያን፤ ክዳትን፡እናስባለን፤ በዚህም፡ሥቃዮችንና፡ታላቅ፡ፍርድን፡እንቀበልበታለን።
፲፫፤ ወለእመ፡ኮኑ፡ይፈቅዱ፡ይስተዩ፡	፲፫፤ ለደዌያቸው፡ፈውስ፡መድኃኒትን፡

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
መድኀኒት፡ ለፈውሰ፡ደዌሆሙ፡ይኤዝዝዎሙ፡ዐቀብተ ፡ ሥራይ ፡ ቀዳሚ ፡ በተሐርሞ፡ ወተከልአ፡እምነ፡ተመጥዎ፡ሕሡማት፡ዘኮነ።	መጠጣት ፡ የሚፈልጉ ፡ ከሆነ ፡ ባለመድኃኒቶች፡አስቀድሞ፡ከሚጎዱ፡ምግቦች፡መከል ከልንና፡መጠበቅን፡ያዟቸዋል።
፲፬፤ ወይቄልጥዎሙ ፡ እምግብር ፡ በዘዘዚአሁ ፡ ተዐግሦ፡በዘይደሉ።	፲፬፤ በየራሱ ፡ መታገሥ ፡ በሚገባው ፡ ሥራ ፡ እንዲወጡ፡ያደርጓቸዋል።
፲፭፤ ወይሜጥኑ ፡ ሎሙ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜያተ ፡ በዘይሰትዩ፡ስቴያተ።	፲፭፤ መጠጣቸውንም ፡ የሚጠጡበትን ፡ ጊዜያት ፡ ሁሉ፡ይወስኑላቸዋል።
፲፮፤ ወጊዜ ፡ ለገቢረ ፡ ምሳሕ ፡ ወጊዜ ፡ ለድቃስ ፡ ወጊዜ ፡ ለዕረፍት ፡ ከመ ፡ ይትወለጥ ፡ ሕዋስ ፡ ክቡድ ፡ ወይትፈታሕ ፡ ሙሓዝ ፡ ግዱድ።	፲፮፤ ለምሳ፡ጊዜ፡ለመኝታና፡ለዕረፍት፡ጊዜ፡ይወስኑላቸዋል ፤ የደነደነው ፡ አካል ፡ ተለውጦ ፡ ይስተካከል ፡ዘንድ ፡ የተዘጋውም ፡ የፈሳሾች ፡ መተላለፊያ ፡ይፈታ ፡ዘንድ።
፲፯፤ ወእምድኅረዝ ፡ ያናሐስዩ ፡ ሎሙ ፡ ኀቢሮታ ፡ እስመ ፡ የአምሩ ፡ ከመ ፡ ፈውስ ፡ ለእመ ፡ ኀብረ ፡ በዘይደሉ ፡ ኢያማስን ፡ አባለ ፡ ዘሥጋ ፡ ወየሀውክ ፡ ደዌያተ ፡ ወመሠረተ ፡ እለ ፡ ይሰትዩ።	፲፯፤ የሕክምናውን ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያቃልሉላቸዋል ፤ መድኃኒቱን ፡ በሚገባ ፡ ካደረጉት ፡ የሥጋን ፡ አካል ፡ እንደማይጎዳ ፡ ያውቃሉና ፡ የሚጠጡትም ፡ መድኃኒት ፡ በሽታዎችንና ፡ መሠረታቸውን ፡ያጠፋላቸዋል።
፲፰፤ ወዜና ፡ ደዌያት ፡ ሕሡማት ፡ ይነውኅ ፡ ተርጕሞታ።	፲፰፤ የክፉ ፡ በሽታዎች ፡ ነገር ፡ ትርጓሜዋ ፡ ይረዝማል።
፲፱፤ ወከማሁ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ዘሪዐ ፡ እከሎሙ ፡ ያቀድሙ ፡ ቅድመ ፡ በአስተንትኖ ፡ ሠናይተ ፡ ምድረ ፡ ወኅሩየ ፡ በሐሪሶታ።	፲፱፤ እንዲሁም ፡ እህላቸውንም ፡ መዝራት ፡ የሚፈልጉ ፡ አስቀድሞ ፡ በማሰብ ፡ መልካሟን ፡ የተመረጠች ፡ ምድራቸውን ፡ በማረስ።
፳፤ ወበአንጽሖ ፡ ርስሐታ ፡ ወበአቀብቅቦታ።	፳፤ እሾኹን ፡ ለቅሞ ፡ በማቃጠልና ፡ በማጽዳት ፡ ደጋግሞ ፡ በማለስለስ ፡ ያደራጃሉ።
፳፩፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይዘርዑ ፡ ዘርዖሙ ፡ ውስቴታ ፡ በተአምኖ።	፳፩፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በውስጥዋ ፡ ዘራቸውን ፡ በእምነት ፡ይዘራሉ።
፳፪፤ ወከማሁ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይትዐየኑ ፡ ነገሥተ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሮሙ ፡ ያቀድሙ ፡ አንጽሖ ፡ ርስሐታት ፡ ወአውዕአ ፡ ጕድፋት ፡ ወኵስ ሐታት	፳፪፤ እንደዚህም ፡ በቤታቸው ፡ ነገሥታትን ፡ ተቀብሎ ፡ ለማስተናገድ ፡ የሚጠብቁ ፡ ቆሻሻውንና ፡ ጉድፉን ፡ አውጥቶ ፡ በመጣል ፡ አካባቢውን ፡ማጽዳትን ፡ያስቀድማሉ።
፳፫፤ ወካዕበ ፡ ይሰፍሑ ፡ መንጸፋተ ፡ ወይሰቅሉ ፡ መንጦላዕተ ፡ ዘብዙኅ ፡ ሜጡ።	፳፫፤ ዳግመኛም ፡ ምንጣፎችን ፡ ይዘረጋሉ ፤ ዋጋው ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ መጋረጃንም ፡ ይሰቅላሉ።
፳፬፤ ወያስተዳልዉ ፡ አጽሕልተ ፡ ወኵስኵስታተ ፡ ወንዋያተ ፡ ኅሩያተ ፡ ወይጸይሑ ፡ ኵሎ ፡ ዐውደ ፡ ማኅደሮሙ ፡ በዘይደሉ።	፳፬፤ ሳህኖችን ፤ ወጭቶችንና ፡ ጌጥ ፡ ያላቸውን ፡ ገንቦችን ፤ የተመረጡ ፡ ዕቃዎችን ፡ ያዘጋጃሉ ፤ የማደሪያቸውንም ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ያጸዳሉ።
፳፭፤ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይረክቡ ፡ ተዘልፎተ ፡ እምነ ፡ መኳንንት ፡ ወመሳፍንት ፡ ወይረግምዎሙ።	፳፭፤ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ከመኳንንቱና ፡ ከመሳፍንቱ ፡ ዘለፋና ፡ ነቀፌታ ፡ ያገኛቸዋል ፡ ይረግሟቸዋል።

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።
፳፮፤ ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ከመዝ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ሰትየ ፡ ፈውስ ፡ ወእለ ፡ ይዘርው ፡ እክለ ፡ ወእለ ፡ ይኄልዩ፡ ምጽአተ ፡ ነገሥት ፡ መዋትያን ፡ ያመጽኡ ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ገድል።	፳፮፤ ለደቂያቸው ፡ መድኃኒት ፡ መጠጣትን ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እህላቸውንም ፡ ለመዝራት ፡ የሚሾቹን ፡ የነገሥታትንም ፡ መምጣት ፡ የሚአስቡ ፡ በዚህ ፡ አምሳል ፡ እንደዚህ፡የሚታገሉና፡የሚተጉ፡ከሆነ።
፳፯፤ ወጽሕቁ፡በአስተንትኖ፡ገድል፡ወይፈርሁ፡ በዐቃቤ ፡ ወይደነግፁ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ እስመ፡እሉ፡ይብሉ፡ይከውንሁ፡ዘኢገበርነ፡ ተሐርሞ፡ዘይደሉ።	፳፯፤ ተጋድኂቸውን ፡ ቦማከናወን ፡ ይተጋሉ፡በመጠባበቅ፡ላይም፡ሁነው፡ይፈራሉ፡ይደነግጣሉም፡ ከዚህም፡በኋላ፡መደረግ፡የሚገባውን፡ጥንቃቄ፡ ያላደረግነው፡ይኖር፡ይሆን፡ይላሉና።
፳፰፤ ወእልክቱ፡ይብሉ፡ነዋ፡ንሕነ፡በጸሐነ፡በአስ ተሐምሞ፡ሐሪሰ፡ምድር፡ወአስተናጽሐታ፡ አምሳለ ፡ ዚአነ ፡ ከመ ፡ ተሀብ ፡ ፍሬያተ ፡ በከመ፡ይደሉ።	፳፰፤ እነዚያም ፡ እነሆ ፡ እኛ ፡ ተግተን ፡ ምድርን፡ በማረስና፡በማለስለስ፡በእኛ፡አምሳል፡ፍሬ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚገባ ፡ ለማድረግ ፡ ደርሰናል፡ይላሉ።
